# Must Read! እውነት ኦሮሚያ የሚለው ስም በታሪክም በተረትም የማይታወቅ የህልም ዓለም ስያሜ ነው?

By Ilma Oromiya

በትምህርትም ሆነ በሀብት ቀና የሚሉ የኦሮሞ ሕዝብ ልጆችን በተለያዩ የፀረ- መንግሥት እንቅስቃሴዎች በመፈረጅ ሲያሳስሩና ሲያስገድሉ የኖሩ የኦሮሞ ፍራቻ-ጥላቻ በሽታ ህመምተኞች በሚያከሂዱት ፀረ- ኦሮሞ ፕሮፓጋንዳ **"ኦሮሚያ የህልም ዓለም ስያሜ ነው፤እስላሞችና ኦሮሞዎች የኢትዮጵያን ሕዝብ ይቅርታ ይጠይቁ፤ ስለኦሮሞ ሕዝብ ጨካኝነት የአገር ውስጥ የታሪክ ጸሐፊዎችና ተመራማሪዎች፤ እንዲሁም የውጭ አገሮች ጸሐፍት መስክረዋል፤ "ጋዳ/ገዳ" የማፊያ ሥርዓት ነው፤ምኒልክና ወታደሮቻቸው ክርስትያኖች ስለነበሩ የአርሲን ሕዝብ ጡትና እጅ አልቆረጡም፤ ይህንን የሚፈጽሙት አረመኔዎቹ ናቸው፤የኦሮሞን አመጽ ይመሩ የነበሩት የወለጋ ፕሮቴስታንቶች ናቸው፤ዛሬ ኢትዮጵያ ለአንድ ኢትዮጵያዊ ሙሉ በሙሉ አገሩ አይደለችም፤ወንድ ልጅን መስለብ የኦሮሞ ባህል ነው፤ኦሮሞ እረኛ ነው፤ ወዘተ…** የሚሉ ከህሙም ህሊናዎች የፈለቁ ፋሽስታዊ ፕሮፓጋንዳዎችን በኢንተርኔትና አገር ውስጥ ታትመው በሚሠራጩ መጽሔቶች እየነዙ ናቸው፡፡ይህን ለመሰሉ የእብደት ቅስቀሳዎች መልስ መስጠት አስፈላጊ ያልነበረ ቢሆንም፤ አንዳንድ የዋህ ዜጎችን ጭምር መልስ መስጠት ያልተቻለና ተረቶቻቸውን እንደመቀበል ሊመስል ስለሚችል የሚከተሉትን አስተያየቶች  መሰንዘሩ ተገቢና አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በጽሑፉም ውስጥ የማንኛውም ሕዝብ ባህልና ታሪክ ላለመድፈር ከፍተኛ ጥንቃቄ የተወሰደ ቢሆንም፤ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ግን ፀረ- ኦሮሞ  ጸሐፊዎች ያቀረቡአቸውን ተረቶች ለማፍረስ ሲባል የቀረቡት መረጃዎች ቅር ሊያሰኙ ስለሚችሉ አስቀድመን ትልቅ ይቅርታ እንጠይቃለን፡፡ በተጨማሪም፤ በአገር ውስጥ የሚታተሙ መጽሔቶች በኦሮሞ ሕዝብ ላይ የሚካሄዱትን የተሳሰቱ ዘመቻዎችን እየተቀበሉና ከኢንተርኔትም ጭምር እየወሰዱ በማተም **(ለምሳሌ ሎሚ መጽሔት)** ሲያሰራጩ፤በሌላ በኩል ግን ሕዝቦችን ከማቃቃር ይልቅ ትክክከለኛውንና እውነተኛውን የታሪክ ግንዛቤ ለማስጨበጥ ተብሎ በተደጋጋሚ የሚላኩላቸውን የመልስ ጽሑፎችን በሁለት ጊዜም ቢሆን እንዲያትሙልን ጠይቀን ለመቀበል ፍቃደኛ ስላልሆኑ በኢንተርኔት ብቻ ለማሰራጨት የተገደድን መሆኑን አንባቢው እንዲረዳልን እንፈልጋለን፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን ውዥንብሮች እንደፈለጉ **""በኢንተርኔትና በሎሚ መጽሔት"** ከሚነዙት ግለሰቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ፤ጋዜጠኛውና በኃይለሥላሴና በተለይም በደርግ ዘመን የግል መኪና ተሰጥቶአቸው ከጋዜጣኛነት በተጨማሪ በኦሮሞ ምሁራንና ነጋዴዎች ላይ የደህንነት ሠራተኛ ሆነው የተመደቡት አቶ ሙሉጌታ ሉሌ እና ተመሳሳይ አመለካከት ያላቸውና ከቡድኑ ጋር በቅርቡ የተቀላቀሉት ዲ/ን ኒቆዲሞስ ዕርቅ ይሁን የተባሉት ናቸው፡፡ በአራተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙት ቀደም ሲል እንደተብራራው **"የሎሚ መጽሔት"** አዘጋጆች ናቸው፡፡ በኦሮሞ ሕዝብ ላይ የሚሰነዘሩትን ተረቶች እየተቀበሉና ከኢንተርኔትም እየለቃቀሙ ከፍተኛ ዘመቻ ማካሄድ እንደጀመሩ በየሳምንቱ ከሚታተመው ጋዜጣቸው መረዳት ይቻላል፡፡

ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ በአዲስ  አበባ ዩኒቨርሲቲ ከሟቹ ከአቶ አለማየሁ ሞገስ ጋር የቅኔ አስተማሪዎች በመባል ተመድበው እነሱ ግን ቅኔውን ማስተማር ትተው ክፍል በገቡ ቁጥር የክፍሉን ተማሪዎች በሙሉ **"በሐጎስና በፈይሳ"** ስሞች እየጠሩና እየቀለዱ ለብዙ የትግራይና የኦሮሞ ተማሪዎች ከዩኒቨርሲቲ መባረር ዋና ምክንያቶች እንደነበሩ በወቅቱ በየኒቨርሲቲ በተለይም በስድስት ኪሎ የነበሩ ተማሪዎች ሁሉ የሚያስታውሱት የቅርብ ዓመታት ሀቅ ነው፡፡ ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ምንም ዓይነት መሻሻል ሳይታይባቸው ከልጅነት እስከ እውቀት የሰይጣን መልእክተኛ ሆነው ሕዝቦችን ለመበታተን ጥረት እያደረጉ ናቸው፡፡ ከቤተ ክህነት ትምህርት ቤት ጀምሮ አብረው ያደጉት ጓደኛቸው ሟቹ ፕሮፌሰር ታደሰ ታምራት ስለንግሥት **ሳባ እና ጉዲት** የፈጠራ ተረቶች፤በ13ኛ

መቶ ክፍለ ዘመን አቡነ ተክለሃይማኖት **ገላንና ያያ** የሚባሉትን ጎሣዎች በመኖሪያቸው በሰሜን ሸዋ ተራራማ ቦታ ላይ እንደ አጠመቁአቸው ወዘተ… **"ቤተ ክህነትና መንግሥት"** በሚለው መጽሐፋቸው ውስጥ በመጥቀስ ፕሮፌሰር ተብየው ጌታቸው ብቻ በግትርነት ጠባያቸው ምክንያት የጥንቶቹን ተረቶች ይዘው ቀሩ እንጂ ብዙዎቹን ምሁራን ግን ከነበራቸው የዜና መዋዕል ውኾንብሮች አላቀው ከዘመናዊ ታሪክ ጋር አስተዋውቀዋል፡፡ እግረ መንገዳቸውንም የኦሮሞ ሕዝብ ጎሣዎች (**ገላንና ያያ** ) በ13ኛ መቶ ክፍለ ዘመን በሰሜን ሸዋ ተራራማ ቦታ ላይ ይኖሩ እንደነበረ ሳይታወቃቸው እውነታውን ገልጸዋል፡፡ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ ቢሆኑ ባሉት ነገር ላይ ረግተው አይቆዩም እንጂ በአንድ ወቅት አስራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የኦሮሞ ሕዝብ ወደ ኢትዮጵያ ግዛት የገባበት አድርገው ሲያወሩ፤ በሌላ በኩል ደግሞ በ13ኛ መቶ ክፍለ ዘመን ኦሮሞዎች በሰሜን ሸዋ ተራራማ ቦታ ከንጉሥ ይኩኖ አምላክ ልጅ ጋር እንደተዋጉና በመጨረሻም ተሸንፈውም ቢሆን አባገዳና አባ ሙዳዎቹ አካባቢውን ለቀው ወደ ደቡብ እንዳፈገፈጉ ጠቅሰዋል፡፡ ይሁን እንጂ አሁን ደግሞ ወደኋላ ተመልሰውና ከአንድ ምሁር ቀርቶ ከማንኛውም ጨዋ አደግ ዜጋ የማይጠበቁ አስጸያፊ ቃላቶችን በሕዝብ ላይ በመወርወር ሕዝብን ለማጋጨት እየቋመጡ ይገኛሉ፡፡ ለመሆኑ፤ከደርግ ጋር የተጣሉትና ጉዳት ደርሶባቸው በዊልቸር መሄድ ደረጃ የደረሱት በዚህ ጠባያቸው ይሆን?

ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የኦሮሞ ሕዝብ ያደረገውን ራስን የመከላከልና የነጻነት ትግል አይቀበሉም፡፡ እንዲያውም **ወራሪ፤ አውዳሚ ወዘተ..** በማለት  የስድብ ናዳ ያወርዳሉ፡፡በሌላ በኩል ደግሞ ራስን ከግዛት አስፋፊዎች በመከላከልና በነጻነት ትግሉ የተቀዳጃቸውን ድሎች ላለመቀበል ሲሉ "**የኦሮሞ ሕዝብ ምንም ሳይዋጋ ግራኝ ባለሰለሱት መንገድ ሰተት ብሎ ገባ** "በማለት ቀደም ሲል **"አውዳሚ"** ያሉትን ረስተው ከአውዳሚነት ነጻ ያደርጉታል፡፡ ለመሆኑ፤ በወቅቱ አገሪቷ የነበራትና የወደሙት ሀብቶችና ቅርሶች ምን ምን እንደነበሩ ለምን ሳይጠቀሱ ታለፉ? ፕሮፌሰር ታደሰ ታምራት ስለወቅቱ አገሪቷ ሁኔታ ሲገልጹ፤ ***ነገሥታቶች በወቅቱ ቋሚ ቤተመንግሥት ስለአልነበራቸው ድንኳኖችን እንደሚጠቀሙ፤የነገሥታቶች ቤተሰብ አባላት፤ ወታደሮች፤የቤተ መንግሥት ሠራተኞች፤ ንብረቶች ከጦር መሣሪያዎች ጭምር አብሮአቸው እንደሚንቀሳቀሱ፤ ከሳር ቤት የተሰሩ ቤተ ክርስትያናት በረጃጅም ርቀቶች ተተክለው እንደሚገኙ፤ የቤተ ክህነት መጽሐፍት ግን በከፍተኛ ጥንቃቄ በየገዳማቱ እንደሚደበቁ በመጽሐፋቸው ውስጥ አብራርተዋል፡፡*** የአክሱም ሀውልቶች፤ በላሊበላ ከአንድ ድንጋይ የተፈለፈሉ ቤተክርስትያናት፤ሌሎችም ጎላ ብለው የሚገኙ ቅርሶች ላይ በ16ኛ መቶ ክፍለ ዘመን በመጀመሪያ ከግራኝ ቀጥሎ ከኦሮሞ ጋር በተደረጉት ጦርነቶች ወቅት እንዳልተነኩ ታሪክ ይመሰክራል፡፤በወርቅ ጉልላትና በወርቅ መስቀሉ ስትደነቅና በወርቅና በዕንቁ እንደተሠራችና በውስጧዋም የአቡነ ተክለሃይማኖት አስከሬን በወርቅ ሣጥን እንደነበረ ሲነገርላት የነበረችው፤በወርቅና በብር የተለበጠ፤ በአልማዝና በእንቁ እንደአጌጠች አውራኢ አቡበከር በሚባለው አንዱ የግራኝ ወታደር እንዳቃጠላት አለቃ አጽሜ (ገጽ 19) ገልጸዋል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ሌሎችም ትላልቅ ቅርሶች በግራኝ ጦርነት ሊወድሙ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ፤እንዲሁ ሀብትና ቅርስ ወደመ ብላችሁ ከምታዳንቁ  እላይ ከተጠቀሱት ውጪ ግራኝ ያወደማቸውን የአገሪቷ ሀብቶችና ቅርሶች ለምን በዝርዝር አላስቀመጣችሁትም? ከግራኝ ጦርነትስ ተርፈው በኦሮሞ የነጻነት ትግል ወቅት የወደሙትን ሀብቶችና ንብረቶችንስ ልትነግሩን ትችላላችሁን? የኦሮሞ ሕዝብ ዓላማ በተደጋጋሚ እንደተገለጸው በ14ኛ መቶ ክፍለ ዘመን የተወሰደበትን አገሩ ለመስመለስ ነበር እንጂ የዋቄፈታን እምነት ለማስፋፋት ስለአልነበረ ቤተክርስቲያንና መስጊዶችን አልነካም፡፡ ኦሮሞ ጠላቱን ሊያሸንፍና የተወሰደበትን መሬት ለማስመለስ የቻለው በገዳ ሥርዓት ከመመራቱ በተጨማሪ በክልሉ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ሲኖሩ ከነበሩት ከራሱ ሕዝብ ያገኘው ከፍተኛ የሆነ ሁለገብ ትብብር እንደነበረ ሊሰመርበት ይገባል፡፡ ይህም በመሆኑ በነዋሪው ሕዝብ ንብረትና ቅርስ ላይ ምንም ዓይነት ጥፋት እንዳላደረሰ ማንም ሰው ሊቀበለው የሚገባ የታሪክ እውነታ ነው፡፡

የኦሮሞ ሠራዊት በጦር ሜዳ ይወጉት የነበሩትን ጠላቶች እየደመሰሰ፤ እጅ የሰጡትን ምርኮኞች **በሞጋሳ ደንብ** መሠረት እየተቀበለ ዓለም እስከ ዛሬ ድረስ ያልደረሰበትን ግብረገብነት እያስተማረ በገዳ ሥርዓት መሠረት በእኩልነት ደረጃ ከራሱ ሕዝብ ጋር አደባልቆ ከሙሉ መብት ጋር እንዲኖሩ አደረገ እንጂ እንደ አንዳንዶቹ ምርኮኞቹን የግል አገልጋዮች በማድረግና እንዳይጠፉም ለመከላከል ቋንጃቸውን አልቆረጠም፤ዘር ኖሮአቸው ከነሱ ሕዝብ ጋር እኩል እንዳይቆጠሩ ወስነው ወንዶቹን  እንዲሰለቡም አላደረገም፡፡

የኦሮሞ ሠራዊት ሲመራ የነበረው በገዳ ማኅበራዊ ሥርዓት ነው፡፡ በመሆኑም፤ የገዳ ሥርዓት ዛሬ ከምንተዳደርበት ዲሞክራሲ ጋር በብዙ መልኩ በጣም ተመሳሳይ ነው፡፡ለዚህ ነው በብዙ መጻሐፍት ላይ የገዳ ዲሞክራሲ እየተባለ የሚገለጸው፡፡የሞጋሣ ደንብ ደግሞ አንዱ የገዳ ሥርዓት መገለጫው ነው፡፡

**ፕሮፌሰር** ጌታቸው ኃይሌ **“እረኝነትንም”** እንደ **“ስድብ”** አድርገው ለመውሰድ ይሞክራሉ፡፡**እረኝነት** ማገድ ወይም መጠበቅ ከማለት ውጪ ሌላ ትርጉም ሊኖረው አይችልም፡፡በመጽሐፍ ቅዱስም **“እግዚአብሔር እረኛዬ ነው”** ሲል ጠባቂዬ ነው ለማለት እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡በማንኛውም አገር ያለው መንግሥት የሕዝቡ እረኛ ነው፡፡በማኅበራዊ ደረጃም እረኝነት የሀብታምነት ምልክት ነው፡፡እያንዳንዱ ግለሰብ በኅብረተሰቡ ዘንድ የሚኖረው ደረጃ በከብቶች ብዛት መጠን ይወሰናል፡፡ በመሆኑም፤ የከብቶች ብዛት የክብር መገለጫዎች ናቸው፡፡ **እረኝነት** ዛሬም በሠለጠኑ አገሮች የሚካሄድ አንዱ የሥራ ዘርፍ ስለሆነ **ፕሮፌሰር ጌታቸው** እንደሚያስቡት የኋላ ቀርነት ምልክት ሊሆን አይችልምና እራሳቸውን ትዝብት ላይ ባይጥሉ ጥሩ ነው፡፡ ኢትዮጵያ በቀንድ ከብት ብዛት ከአፍሪካ አንደኛ ነች እየተባለች የክብር ቦታ የተሰጣት **ፕሮፌሰር ጌታቸው** እንደሚያስቡት ሳይሆን  እንደማንኛውም የዓለም ሕዝብ እጅግ በጣም በተከበረ የሥራ ዘርፍ በመሰለፍዋ መሆኑን ሊያውቁት ይገባል፡፡በ16ኛ መቶ ክፍለ ዘመን ቀርቶ ዛሬም በ21ኛ መቶ ክፍለ ዘመን ብዙ ሕዝብ በእረኝነት እየተዳደረ መሆኑን መዘንጋት የለብንም፡፡የኦሮሞ ሕዝብ ብዙ ከብቶች ስለአሉት ከእርሻው በተጨማሪ እረኝነትን እንደ አንዱ ሥራው አድርጎ የሚጠቀም፤ከልመና የፀዳና ከራሱ አልፎ ለሌላውም የሚተርፍ ባለቅቤ፤ባለወተትና የጮማ ጌታ ነው፡፡ እረኝነት የተለያዩ ባለሀብቶች በተለይም ወጣቱም ትውልድ በዘመናዊ አያያዝ ዘዴ እየተጠቀሙበት ሕይወታቸውን የሚመሩበት ትልቅ ክብር ያለው የሥራ ዘርፍ ነው፡፡ በዚህም የተነሳ ከብት ማድለብ፤ የወተት ከብቶችን ገዝቶ መጠቀም በብዙ አካባቢዎች እየተሰራበት ይገኛል፡፡ በዓለም አስነዋሪ ድርጊቶች መካከል አንዱ ግን **ልመናን** እንደ ባህልና እንደ ሥራ መቁጠሩ ላይ ነው፡፡ በየመንደሩ እየዞሩና በየቦታው እየተቀመጡ በመለመን ሕዝብን ማስቸገር እጅግ በጣም አሳፋሪና የአእምሮ ድቀት ውጤት መሆኑን፤ እረኝነት ግን እጅግ በጣም የተከበረ፤ የዓለም ሕዝብ የተቀበለውና የሚተዳደርበት አንዱ የሥራ ዘርፍ መሆኑን ለይተን ሊናውቀው ይገባል፡፡ በህክምና የሚዳን በሽታን የእግዚአብሔር ቁጣና ትእዛዝ እየተደረገ **“ካልለመን እንቆመጣለን”** እየተባለ ሌሊት በየመንደሩ እየዞሩ በልመና ስም በመጮህ ነዋሪውን ሕዝብ፤ አራሹን ገበሬ፤ ከብቶቹን ሲጠብቅና ሲደክም የዋለውን እረኛ እንቅልፍ መንሳት ፤ **“*ሥራ ቢጠፋ ለምኜ እበላለሁ*”** በሚል ከንቱ ፈሊጥ በየጸሎት ቤቶች አካባቢ መኮልኮል፤ወዘተ..ሊወገዱ የሚገቡ የኋላቀርና የአእምሮ ድቀት ምልክቶች ናቸው፡፡በአገር ደረጃም ሆነ በግለሰብ ደረጃ ልመና እጅግ በጣም የተናቀና እራስን ያለመቻል ምልክት ስለሆነ በዓለም ደረጃ እየተወገዘ ይገኛል፡፡ በመሆኑም፤ *መሥራት*፤ *መሥራት* የየእለቱ መፈክራችን መሆን አለበት፡፡***ሥራ*** የእድገት ምልክት ስለሆነ ያስከብራል፤ **ልመና** ግን ከአእምሮ ድቀትና ባዶነት የሚመጣ ትልቅ ደዌና የድህነት ምልክት ስለሆነ ያሳፍራል፤ ያስንቃል፡፡

ኦሮሞ **ነባር ሕዝብ** እንጂ የፎቢያ ሕመምተኞች እንደሚሉት “**ክርስቲያኑ በሩን ከፍቶለት ሰተት ብሎ የገባ**” አይደለም፡፡ የኦሮሞ ሕዝብ የአፍሪካ ነባር ሕዝብ እንደሆነ (ዳረል ባትስ፤1979)፤ቀደም ሲል በአክሱም አካባቢ ይኖር እንደነበረ (ፕርሃም 1948) በስፋት አብራርተዋል፡፡ሌሎቹም ምሁራን ደጋግመው የገለጹት ቢሆንም የሚከተሉትን እንመልከት፡፡

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን መጽሔት (ቁጥር 2፤ 2012) የደራሲና የታሪክ ምሁሩ ተክለጻድቅ መኩሪያን መጽሐፍ (የኢትዮጵያ ታሪክ፤ ከዐጼ ልብነ ድንግል እስከ ዐጼ ቴዎድሮስ፤ 1961) በመጥቀስ ስለኦሮሞ ሕዝብ ነባርነት ሲገልጽ፤

> **”ኦሮሞዎች የካም/ኩሽ ዘሮች መሆናቸውን ጽፈው ወደ ኢትዮጵያ የገቡት በዐጼ ልብነ ድንግል ዘመን(እ.ኢ.አ 1500-1530) ነው የሚሉትን ድርሳናት አጥብቀው በመቃወም የሴም ዘር የሆኑት ነገደ ዮቅጣን (አግዓዝያን) ወደ ኢትዮጵያ ከመግባታቸው በፊት እንኳ የካም/ኩሽ ዘር ኢትዮጵያ ውስጥ እንደነበር ያረጋግጣሉ”**ብለዋል፡፡
>
> **ክንትሮሲኒ** ንጉሥ አምደጽዮን **(1314-1344) በወታደሮቻቸው ውስጥ በአብዛኛው ኦሮሞዎችን ይመለምሉ ነበር** (Oromo of RaYYa and Zobel-Napols- 1938. Pp- 11-14) በማለት ገልጸዋል፡፡
>
> በሰሜኑ ኢትዮጵያ ለዘመናት ሲደርስበት የነበረውን ጭቆና ተቋቁሞ ለዛሬው ስለደረሰው
>
> ስለ አዘቦ ራያ ኦሮሞ ታሪክ **በገድለ ማርቆሪዎስ** (Vol.22.PP 15-18) እንዲህ ይላል፡፡”
>
> **በ14ኛ መቶ ክፍለ ዘመን የአዘቦ ራያ የገዳን ሥርዓት ያከብር ነበር**”፡፡
>
> በተጨማሪም እራሳቸው ፕሮፌሰር ተብየው አቶ አጽሜና አለቃ ታዬም ኦሮሞ በ16ኛው
>
> መቶ ክፍለ ዘመን መጣ እንዳላሉ ከመጻፍ አልፈው በተለይም አለቃ ታዬ **ኦሮሞ ወደ**

**ኢትዮጵያ የገባው በዘጉዌ ዘመን በዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነው** የሚሉትን ሀተታ

በሌሎች ቦታዎች ቢሰርዙም **የአባ ባሕርይ ድርሰቶች ከሌሎች ኦሮሞን የሚመለከቱ**

**ጽሑፎች** ጋር በሚሉት የፎቢያ ሕመምተኛ መጽሐፋቸው ውስጥ ግን አስፍረዋል፡፡

ከላይ የተጠቀሱት መረጃዎች ሁሉ ነባርነቱን እንጂ በ16ኛ መቶ ክፍለ ዘመን በር ተከፍቶለት የገባ አለመሆኑን ነው፡፡

በተጨማሪም በዚሁ በተረጎሙት መጽሐፍ ላይ (ገጽ 87-89)

**በጦርነቱ ወቅት "ንጉሡ የጋሎችን/ኦሮሞዎችን ራስ እንዲቆራርጡ ለወታደሮቻቸው ትእዛዝ ሰጡ፤የተቆረጠው ራስ ሰፊውን ቦታ ሞላው፤የድል መንፈስ ያሳረፈውን**

**እግዚአብሔርንም አመሰገኑ"** በማለት ይጠቅሳል፡፡

ከዚህም መረጃ የምንረዳው ጦርነት እንደነበረ እንጂ በፈቃደኛነት ያስገቡአቸው እንዳልሆነ ነው፡፡ ታዲያ፤ ይህ አባባልዎ **"ክርስትያኑ በሩን ከፍቶለት ሰተት ብሎ ገባ" ፤በሌላ ቦታ ደግሞ"አውዳሚ"** ከሚሉት ተረቶች ጋር እንዴት ይሄዳል? በእውነቱ ሥራዎ ኅሊና ላለው ሰው እጅግ በጣም የሚያሳፍር ነው፡፡ ለማንኛውም የኦሮሞ ሕዝብ ነባር ሕዝብ እንደሆነ፤ የ16ኛ መቶ ክፍለ ዘመን ጦርነትም የተወሰደበትን አካባቢ በጉልበቱ አሸንፎ ያስመለሰበት ጊዜ እንጂ በፈቃደኛነት በር ተከፍቶለት የገባ መጤ ሕዝብ እንዳልሆነ ፕሮፌሰር ተብየው ጌታቸው ብቻ ሳይሆን ማንም ሰው ሊያውቀው የሚገባ የታሪክ ምስክርነት ያገኘ እውነታ ነው፡፡

ፕሮፌሰር ጌታቸው ስለ **ገዳ** ምንነት ለማወቅ ስላልፈለጉ በደፈናው **ሕግ አልባ፤ በጭፍን የሚጓዝ የማፊያ ጥርቅም** ነው በማለት ተገቢ ያልሆኑና መረጃ -አልባ አስተያየቶችን ሰንዝረዋል፡፡ሌቪን (Levin D, Greater Ethiopia, 1983) **"ትልቋ ኢትዮጵያ"** በሚለው መጽሐፋቸው በ16ኛ መቶ ክፍለ ዘመን በኦሮሞዎችና በክርስቲያኑ መካከል በተደረገው ጦርነት ላይ የዓይን ምስክር የነበሩትን ወታደርና የካቶሊክ ቄሶችን በመጥቀስ **"የኦሮሞ ተዋጊዎች እንደ ማንኛውም የሠለጠነ ጦር በተደራጀ አቋም ወደ ጦርነት ገብተው ወዲያውኑ በክርስቲያኑ ጦር ላይ ከፍተኛ ጉዳት አደረሱ"** በማለት የሰጡት ምስክርነት፤ እንዲሁም የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ጥናት መጽሔት ቁጥር 2፤2012 ላይ የኢሬቻ በዓል ልዩ እትም 2008 መጽሔትን በመጥቀስ በ16ኛ መቶ ክፍለ ዘመን የተደረገው የኦሮሞ እንቅስቃሴ **"አዲስ መከሰት"** ሳይሆን **የተነጠቀ** አገሩን ለማስመለስ የመልሶ ማጥቃት ዘመቻ ያደረገበት ጦርነት (war of resistance) እንደነበረ መግለጻቸው ድርጊቱ በጠላት ወገን እንደተጠቀሰው ሳይሆን በሕግና በዓላማ ላይ የተመሠረተ ለመሆኑ ማረጋገጫዎች ናቸው፡፡በተጨማሪም፤ኢትዮጵያዊያኖቹ ሎሬት ጸጋዬ ገብረ መድኅን ቀዌሳና ደራሲው ተክለጻድቅ መኩሪያ፤ እንግሊዛዊው ፕላውዴን፤ፈረንሣዊው ዲ አባዲ፤ኤርትራዊው ፕ/ር አስመሮም ለገሠ ሌሎቹም ብዙ ምሁራን በገዳ ሥርዓት ላይ ሰፊ ጥናት አድርገው **ስለገዳ ሥርዓት ዲሞክራሲያዊነት ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል፡፡ እንዲሁም የገዳ** ሥርዓት አንዱ የአፍሪካዊ ቅርስ ሆኖ በዩኒሴፍ እንዲመዘገብ አስተያየታቸውን በጽሑፍ ያስቀመጡ ብዙ ምሁራን አሉ፡፡ በሌላ በኩል ግን፤ፕሮፌሰር ጌታቸው **ገዳ "የማፊያ ጥርቅም ነው"** በማለት ከሲሲሊ(ጣሊያን) የወሮበሎች ድርጅት ጋር ለማመሳሰል ሞክረዋል፡፡ የሚያሳዝነው ግን በቦታ፤በዘመን፤በተግባር ወዘተ…እንደማይገናኙ አለማወቃቸው ነው፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ትልቅ ክብር ባላቸው ምሁራን ሳይንሳዊ ጥናት ተደርጎ ምስክርነት ያገኘውን የገዳ ሥርዓት በግል ስሜት ተነሳስቶ ያለአንዳች ጥናት ስሙን ለማጉደፍ መሞከር ትርፉ ትዝብት እንጂ ምንም ዓይነት ጥቅም እንደማይኖረው ሊታወቅ ይገባል፡፡ በብዙ የዓለም ምሁራን የተመሰከረለትን ሕዝባዊ አደረጃጀት (ገዳን) ከህቡዕ የወሮበሎች ድርጅት ጋር ማወዳደር ከአንድ ምሁር ሳይሆን ከህሙም ኅሊና ብቻ የሚፈልቅ ተራ አመለካከት ነው፡፡

ፕሮፌሰር ጌታቸው አንዳንድ አስጸያፊ ስድቦችን ከመወረወር ውጪ በጥልቀት ስለተናገሩት ጉዳይ እንኳን በሥርዓት የሚያስረዱ ነጥቦች የላቸውም፡፡ ይህ በእውነቱ ትልቅ በሽታ ነው፡፡ የዚህ ዓይነቱ በሽታ ደግሞ በመማርም ሆነ በእድሜ ባለጸጋነት የሚለቅ ሳይሆን እስከ እለተሞት ድረስ አብሮ የሚሄድ ትልቅ ደዌ ነው፡፡ በዚህ ዓይነት በሽታ ተጠምደው

በሞት አፋፍ ላይ ከሚገኙት ውስጥ አንዱ እራሳቸው ፕሮፌሰር ጌታቸው በመሆናቸው እጅግ በጣም ያሳዝናል፡፡ ሁለተኛው በዚህ በሽታ የተለከፉት **“የፖለቲካው ታንታኝ ነኝ”** ባዩ አቶ ሙሉጌታ ሉሌ ናቸው፡፡በሽታው ከሁሉም በላይ ይሉኝታ የሚባለውን ትልቁን የሞራል ክፍል ይደመስሳል፡፡ ለዚህም ነው ፕሮፌሰር ጌታቸው የፖለቲካ ተንታኙ በጋራ ሆነው በአንድ ሕዝብ ላይ ቀርቶ በግለሰብ ላይ እንኳን ለመጠቀም እጅግ በጣም አሳፋር የሆነውን ስድብ በኦሮሞ ሕዝብ ላይ ለመጠቀም ከፍተኛ ድፍረት ላይ የደረሱት፡፡ **“የወንዶችን ብልት መስለብ የኦሮሞ ባህል ነው”** ብለዋል፡፡ የገዳ ሕጎች በአንዳንድ ኦሮሞዎች አካባቢ ወይም በአያንቱዎች ዘንድ በቃል ሲወርድ ሲዋረድ የመጡ ካልሆኑ በስተቀር ሌሎቹ ቀደም ሲል በሚሲዮናውያን ተጽፈው የነበሩት በአብዛኛው በገዥው መደቦች ትእዛዝ እንደወደሙ ታሪክ ይመሰክራል፡፡ በኋላ ላይ ግን እነዚህ የወደሙ ሕጎች በተወሰኑ የሕግ ተማሪዎች ተሰብስበው በየዩኒቨርሲቲው ለመመረቂያ ጽሑፍነት አገልግሎት መዋላቸው ይታወቃል፡፡ ከነዚህም ውስጥ አንዱ የአቶ ዲንሳ ሌጽሳ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የመመረቂያ ጽሑፍ አብዛኞቹን የኦሮሞ ሕጎች ይዟል ማለት ይቻላል፡፡ በነዚህና ከዚያም በኋላ በቀረቡት ጥናቶች ውስጥ በየትም ቦታ ከላይ የተጠቀሰው ድርጊት በኦሮሞ ባህላዊ ሕጎች ውስጥ አልተጠቀሰም፤ ተጠቅሶም አያውቅም፡፡ በክርስቲያን መኖሪያ አካባቢ በጉርብትና የሚኖረውን አንድን የኦሮሞ ጎሣ እንዲጨርሱ ወገንተኛው መንግሥት ለክርስቲያኑ ወገን **“ለዝንጀሮ መከላከያ ነው”** እያለ በየጊዜው መሣሪያ ያስታጥቅ እንደነበረ ምስክርነት የማይጠየቅበት በእድሜአችን ያየናቸው የጥፋት ድርጊቶች ነበሩ፡፡ በዚህ አካባቢ የሚኖረው ሕዝብ እራሱን ለመከላከል የፈጠረው የሕይወት ማዳኛ ዘዴ ነበር እንጂ የመላ ኦሮሞ ባህል ሆኖ አይደለም፡፡ ይህ አመለካከት እጅግ በጣም ኋላቀር አስተሳሰብ መሆኑን ሊታወቅ ይገባል፡፡ ይህ አባባል በምንም ዓይነት ትክክል እንዳልሆነ ከፕሮፌሰር ተብየው ይልቅ **የፖላቲካ ተንታኝ ነኝ** ባዩ አድገው ለሥራ አዲስ አበባ እስከገቡ ድረስ የኖሩት በኦሮሚያ ክልል ውስጥ ስለነበረ ቢያንስ በኖሩባቸው አካባቢዎች የዚህ ዓይነቱ ድርጊት እንደልተፈጸመ ምስክርነት ባይጠበቅባቸውም አንዱ ተሳዳቢ ሆነው መቅረባቸው ግን እጅግ በጣም ያሳዝናል፡፡ሌላው ቢቀር ብዙ የቅርብ ዘመዶቻቸው አሁንም በወለጋ ውስጥ ከኦሮሞ ሕዝብ ጋር አንድ ሆነው በሰላም እየኖሩ እንደሚገኙ መዘንጋት አልነበረበትም፡፡በየጊዜው ከተለያዩ የአገሪቷ ክልሎች እየመጡና በየገጠሩ ኦሮሚያ እየገቡ በነፃነት እየሠሩና በሰላም ወደ አካባቢያቸው የሚመለሱበት ሕዝብ ሁኔታ እያየን **“መስለብ የኦሮሞ ባህል ነው”** የሚለው አባባል በታኝና አስነዋሪ ጉዳይ መሆኑን ሊታውቁት ይገባል፡፡ ድህነታችሁ በይሉኝታ ማጣት ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ አእምሮ ጭምር በመሆኑ እጅግ በጣም ያሳዝናል፡፡እስከዛሬ ድረስ በዓለም ላይ **“ብልት መስለብ”** የሕዝብ ባህል ሆኖ አይታወቅም፡፡ ነገሥታቶች ግን አንዳንድ ጊዜ ኃይለኛነታቸውን ለማሳወቅ ሲሉ ማንኛውንም ዓይነት ግፍ ይፈጽማሉ፡፡ ለምሳሌ፤ የሸዋው **ነጋሢ ክርስቶስ(1696-1703)** ጎንደር አጼ ፋሲል ዘንድ እያሉ እንደሞቱ ልጃቸው**ሰብስቴ(1703-1720)** የአባታቸውን ቦታ መያዛቸውን ሾላ ሜዳ በሚባለው ቦታ ሕዝብ ሰብስበው አዋጅ እንዳስነገሩ **አለቃ አጽሜ** ይገልጻሉ፡፡

**የመንዝ ሰው ተከተለኝ፤ስሜም መርዕድ አዝማች ነው፤**

**መርዕድ አዝማች ያላልኸኝ፤ ሴት ልጅህን ጡቷን፤**

**ወንድ ልጅህን ብልቱን እሰልበዋለሁ፡፡**

ይህ አዋጅ የታወጀው በ18ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ (እ.ኢ.አ.1704) ሲሆን፤ **ወሰን ሰገድ(1808-1813)** ደግሞ የአባቱን **የአስፋ ወሰንን** አልጋ ከያዘ በኋላ **አንጎለላ** በሚባለው ቦታ ድረስ መጥተው ፤ሕዝብ ሰብስበው “**እኔ ወይዘርነት አለኝና ራስ በሉኝ፤ ራስ ወሰን ሰገድ** ያላለኝን **ሴት ልጅህን ጡቷን፤ወንድ ልጅህን ብልቱን እሰልበዋለሁ”** በማለት አዋጅ አውጥተዋል፡፡ ሁለቱም አዋጆች የታወጁት ለሚያስተዳድሩት ሕዝባቸው መሆኑ ሊታወስ ይገባል፡፡ ምኒልክ ደግሞ በማዕረግ ጉዳይ ሳይሆን አልገብርም ባሉት ሕዝቦች ላይ ጡት ቆረጣንና የብልት ሰለባውን እርምጃ ወስዷል፤ ለምሳሌ፤ በ1886/7 ባካሄዱት የአርሲ ወረራ ላይ ተጠቅመውበታል፡፡ በዚህ ጊዜ መሀከልም ብዙዎቹ ተግባራዊ ሲያደርጉት ቆይተዋል፡፡ ስለዚህ፤ እላይ የተጠቀሱት አዋጆች **“ምኒልክና ራስ ዳርጌ ክርስቲያኖች ስለሆኑ እንደዚህ ዓይነት ድርጊት አይፈጽሙም፤ጡት መቁረጥ የአረመኔዎች ድርጊት ነው”፤”ብልት መስለብ የኦሮሞ ባህል ነው”** ለሚሉት የፍራቻ ጥላቻ በሽታ ህመምተኞች ምን ያህል የተሳሳቱና የራሳቸውን ጉድ እንኳን የማያውቁ ለመሆናቸው በቂ መረጃዎች ናቸው ፡፡ ለማንኛውም፤ በትክክል ማለቴን አላውቅም እንጂ “የእምዬን **ለአብዬ” የሚል ጥሩ አባባል እንደላ አስተውሳለሁ፡፡ በቤተ መንግሥታቸው ውስጥ በአገልጋይነት የሚመደቡት ወንዶች በአብዛኛው ስልብ የነበሩትን አጼ ምኒልክ አያውቁአቸውም ማለት ይቻላልን**?

ፕሮፌሰር ጌታቸው በቅርቡ **የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን** ላይ ቀርበው እድሜዬ ትልቅ ነው፤አርጅቼአለሁ፤ጠረጴዛዬን በመጠራረግ ላይ ነኝ፤ ምንም ነገር መሥራት አልችልም፤ሞትን እየተጠባበቅሁ ነኝ ሲሉ ሰምቼ በጣም አዘንኩ፡፡ ተምሬአለሁ የሚሉትና ሥራቸው ግን ከጥንት ደብተራዎች የማይሻልና አንድ ቀን እንኳን በታሪክነት የሚቀመጥ ጽሑፍ

አቅርበው ሳያውቁ ሞትን እየጠበቁ መገኘታቸው እጅግ በጣም ገረመኝ፡፡ ከንቱ ኑሮ ማለት ከዚህ በላይ ምንድነው? አባ ባሕርይ ሰነድ፤የተክለ ሥላሴ ጢኖንና የተክለ ማርያም ዋቅጂራ የጻፉት ዜና መዋዕል ስለአነበቡ የኦሮሞን ታሪክ አውቃለሁ ብለው ይደነፋሉ፡፡ አንዳንዶቹም የኦሮሞ ስም ስለያዙም ኦሮሞ አድርገው ለማቅረብ ይሞክራሉ፡፡ እንዲያውም፤ ሲራቀቁ **"የኢትዮጵያን መንግሥት ተወደደም ተጠላ ያቋቋሙት ክርስቲያኖች ነበሩ"** በማለት በድፍረት ሲያቀርቡ መቼ እንደተቋቋመ ግን ሳይጠቅሱት አልፈዋል፡፡ እውነት ይህ አባባል ከአንድ የቤተ ክህነት ምሁር እየተደረጉ **በኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን** ከሚቀርቡትና ከልጅነት እስከ እውቀት በአገር ውስጥና ውጭ አገር ስለዚሁ ሲማሩ ከኖሩት ፕሮፌሰር ጌታቸው አንደበት የሚወጣ ነው? ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ የገባው ከክርስቶስ ልደት በኋላ በአራተኛ መቶ ክፍለ ዘመን መሆኑ ዓለም የሚያውቀው የታሪክ እውነታ ነው፡፡ ታዲያ፤ የኢትዮጵያ መንግሥት ከክርስቶስ ልደት በኋላ ከአራተኛ መቶ ክፍለ ዘመን በፊት አልነበረም ማለት ነው? የአክሱም መንግሥትስ መቼ ነው የተቋቋመው? በእውነቱ ክርስትናን ከኢትዮጵያ መንግሥት በፊት ማስቀደሙ ትልቅ ስህተት ስለሆነ ሊታረም ይገባል፡፡

አቶ ሙሉጌታ ሉሌ ኢህአዴግ እንደገባ **"አጥፍቶ መጥፋት"** የሚል የክህደት መጽሐፍ ጽፈው ለኢህአዴግ እጅ መንሻነት አቅርበው ነበር፡፡ ግን መጥፎ ሥራቸው ጎልቶ ይታወቅ ስለነበረ ተቀባይነት አላገኙም፡፡ መጽሐፋቸውንም ባሳደጉት ልጅ ስም ደራሲው "**ዮሐንስ**" ብለው አወጡ፤ በየጋዜጣው ግን የሚጽፉት በአብዛኛው **"ስንሻው ተገኝ"** በሚል የብዕር ስማቸው ሲሆን፤ ሌሎችም የብዕር ስሞች እንዳላቸው ይታወቃል፡፡ አነግ ከኢህአዴግ መንግሥት ጋር በነበረበት ወቅት የሌንጮ ለታ አስተማሪ እንደነበሩ ለመግለጽ በየጊዜው **"ስንሻው ተገኝ"** በሚል የብዕር ስም ይጠቀሙ እንደነበረ የወቅቱን ጋዜጦችን አይቶ መረዳት ይቻላል፡፡ **አነግ** ከሄደ በኋላ ደግሞ የእውቁ **ሎሬት ጸጋዬ ገብረ መድኅን ቀዌሳን** ስም ወስደው "**ጸጋዬ ገብረ መድኅን አርአያ**" እያሉ ሲቀባጥሩ እንደነበረ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው፡፡ ሰሞኑን ደግሞ አቶ ሌንጮ ለታ "**የኦሮሞ ዴሞክራሲያዊ ግንባር የሚባለውን አዲሱን የፖለቲካ ድርጅት በማቋቋም ወደ አገር ቤት ተመልሰው ለመታገል ዝግጅታቸውን አጠናቀዋል**" የሚል ዜና በአንዳንድ ጋዜጦችና መጽሔቶች በሚተላለፍበት ወቅት አስተማሪአቸው እንደነበሩ አዲስ ዜና አድርገው እያቀረቡልን ናቸው፡፡ አቶ ሙሉጌታ፤ በአንድ በኩል ኦሮሞ "**አረመኔ**" ነው እያሉ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ሌንጮ ለታን መሰላል አድርገው ወደ ሥልጣን የሚሄዱበትን የሕልም መንገድ እየጠራረጉ መሆናቸውን እያሳዩን ናቸው፡፡

አቶ ሙሉጌታ ሉሌ ዛሬ አሜሪካ አገር ተቀምጠው በኢትዮጵያ **ሳተላይት ቴሌቪዥን "የፖለቲካ ተንታኝ ነኝ"** ቢሉም አመለካከታቸው ግን ከጥንቱ ከፊውዳል አስተሳሳብ አንድ ስንዝር እንኳን ፈቀቅ አላለም፡፡ የዲሞክራሲ ቁንጮ ተደርጋ በምትታየው አሜሪካ እየኖሩ ስለ የግልና የቡድን መብቶች ምንነት እንኳን ሊነግሩን ቀርቶ የአንድ አገር ብሔርና የክልሉ መጠሪያ ለምን ከፊውዳል ሥርዓቱ አጠራር ይቀየራል በማለት እየተሟገቱ ናቸው፡፡ የኦሮሞ ሕዝብ ጥንትም ቢሆን እራሱን የሚጠራው **ኦሮሞ**፤ አገሩን **ኦሮሚያ** እያለ ነው፡፡አቶ ሙሉጌታ ግን እኔ ይህንን ስም ቅርብ ጊዜ ፕሮፌሰር አስመሮም ለገሠ ከጻፉ በኋላ ነው ያወቅሁት፤ ከዚያ በፊት የማይታወቅ ስም ስለሆነ ይቅርባችሁ፤ እንደ ጥንቱ **"ጋላ"** ተብላችሁ ብትጠሩ ይሻላል፤**"ጋላ"** ማለት ስድብ ሳይሆን **"ትልቅ"** ማለት ነው በማለት ከአርባ ዓመታት በፊት አሽቀንጥሮ የጣለውን ስም እንደገና ሊመርጡለት ይሞክራሉ፡፡ **ድንቄም የፖለቲካ ተንታኝ**፤ለመሆኑ **"ጋላ** "የሚለው ቃል ትርጉሙ በአማርኛ **"ትልቅ"** ማለት ነው ያሉት ቃሉ ከምን የመጣ ሆኖ ነው? ከግዕዝ፤ከግሪክ፤ ከአገው፤ ወዘተ…የምን ቃል እንደሆነ ለምን አልጠቀሱም? አሜሪካ አገር ተቀምጠው ስለዲሞክራሲ እያወሩና ለሰው ልጆች መብት ተከራካሪ ነኝ እያሉ፤ በሌላ በኩል ደግሞ የኦሮሞ ሕዝብ እራሱን የሚጠራበትን ስም ትክክል ስለአልሆነ እኔ በምመርጥለት ስም ቢጠራ ይሻላል ሲሉ ትንሽ እንኳን እፍረት አይሰማዎትምን? ለማንኛውም አጉል ድፍረትዎ የአስተሳሰብ ባዶነትን በደንብ የሚያስረዳ ስለሆነ ምንም አይደንቅም፤ ይልቁንም የሚያሳስበኝ የትምህርት ደረጃዎ ያው የምናውቀው ነው ወይስ ተሻሽሏል? የሚለው ጥያቄ ነው፡፡

አቶ ሙሉጌታ ሉሌ እዚህ በነበሩ ጊዜ ስለእራሳቸው አማራነት ሲናገሩ "የእኔ ወላጆች ጎጃሜዎችና መርሐቤቴዎች ናቸው" ይሉ ነበር፡፡ የጎጃም ሕዝብ **"ከጋላ/ኦሮሞ ያልተወለደ ደበን አንሳ** *ነው"* *ስለሚል እዚህ ላይ የእርሳቸውን ምርጫ አላውቅም፡፡ ስለመርሐቤቴ ግን* አቶ ግርማ አውግቸው ደመቀ (ገጽ 25) **የአማርኛ ቋንቋ አጀማመር** በሚለው መጽሐፋቸው የቸርኔትሶቭ(Chernetsov; 1993;101) መጽሐፍ በመጥቀስ የሚከተለውን አስቀምጧል፡፡ "**አብዛኛው የመርሐቤቴ ሕዝብ ከፍቼ አካባቢ የሄዱ ኦሮሞዎች ናቸው ፡፡ ቀደም ሲል አማርኛን አይናገሩም ነበር፡፡ በኋላ ላይ ግን አማርኛ መናገር ቻሉ፤ ቀስ በቀስም እራሳቸውንም እንደ አማራ መቁጠር ጀመሩ" ብለዋል ፡፡** ስለዚህ፤ አቶ ሙሉጌታ፤የራስዎን ማንነት እንኳን በትክክል ለይተው የማያውቁ ግለሰብ ሆነው ለኦሮሞ ሕዝብ ስም ለመምረጥ እንዴት ይችላሉ? መታሰቡ እራሱ በጣም የሚገርምና፤እጅግ በጣም የሚያሳፍርም ነው፡፡ መጀመሪያ የራስዎን ማንነት በደንብ ለይተው ማወቁ ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል፡፡

አቶ ሙሉጌታ፤ የታሪክ አዋቂና ተቆርቋሪ ለመምሰል የሌሎች አገሮችን መሪዎች፤እንዲሁም ሽፋኑን እንጂ የውስጡን ይዘት አንብበው የማያውቁትን የመጻሕፍት ደራሲያን ስሞች በማያስፈልጉ ቦታዎች ሁሉ ከመስንቀር ያለፈ እርባና ያለው ትንታኔ አያቀርቡም፡፡ የተረት አቀራረባቸው ታሪክ የሆነላቸው እየመሰላቸው በተለይም **ጆርጅ ኦርዌልን** በምንም ዓይነት ሳይጠቅሱአቸው አያልፉም፡፡ በዚህም ምክንያት ይመስላል የልብ ልብ ተሰምቶአቸው **"ታሪክ ድርሰት ሆነ"** ብለው አዋቂነታቸውን ለማስመስከር ጥረት የሚያደርጉት:: ለመሆኑ: በአቶ ሙሉጌታ ጽሐፎች ውስጥ፤ታሪክና ድርሰት ተለይተው ይታወቃሉን? እስቲ፤ የጻፉአቸውን መለስ ብለን እንመልከታቸው፡፡አጼ ምኒልክን ለመካብ የራሳቸው እውነተኛ ታሪክ በቂ ሆኖ እያለ አጼ ዮሐንስ ከጎጃሙ አስተዳዳሪ ጋር በተዋጉበት ወቅት ምኒልክ የሚከተሉትን ሊናገሩ ቀርቶ በቦታውም እንዳልነበሩ እየታወቀ **"እባክዎን ጃንሆይ ከንጉሥ ተ/ሃይማኖት ጋር ስለተጋጩ ሕዝብዎን አያስጨርሱ"** በማለት ለመኑአቸው ብለው ጻፉ፡፡ ከየት አመጡት ቢባሉ ምን ሊሉ ነው? አሜሪካ መሆንዎ በጀዎት እንጂ እዚህ ቢሆኑ ኖሮ የውርደት ሸማ ይከናነቡ ነበር፡፡ አላዋቂነት ደፋር ያደርጋል የሚባለው እውነት ሆነ ማለት ነው፡፡ እንደፈለጉ ከኪስዎ ውልቅ እያደረጉ የሚጽፉት ሁሉ ለድርሰትነት እንኳን የማይበቃ ተራ ሌብነት እንደሆነ ትንሽ እንኳን እንዴት አይታወቅዎትም? ሌላው ቢቀር ቀደም ሲል የጎጃም ባላባቶች ንጉሥ እንደማይባሉ፤ለመጀመሪያ ጊዜ ግን አጼ ዮሐንስ ራስ አዳልን **ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት**አሰኝተው እ.ኢ.አ በ1873ዓ. ም እንደሾሙአቸው አቶ ሙሉጌታ እንዴት አያውቁም? **የወላይታው ንጉሥ ካዎ ጦና፤የጂማው ንጉሥ አባጅፋር፤ የወለጋው ደጃዝማች ገብረ እግዚአብሔር** ያላሉትንና በታሪክ ቀርቶ በተረት ደረጃ እንኳን ተወርቶ የማይታወቀውን እንዴት ለሕዝብ ያቀርባሉ? እውነት ጓድ መንግሥቱ ኃይለማርያም **"እኔ ዳግማዊ ቴዎድሮስ ነኝ"** ብለዋል? የት ቦታ? ፈጽሞ አላሉም፤አይሉምም፡፡ አንድ ጊዜም ጊዜያዊ የሆነ ርካሽ ክብር ያገኙ መስሎዎት ከፕሬዚዳንት መንግሥቱ ኃይለማርያም ጋር **"አንዳንድ ቀን ምሳ አብረን እንበላ ነበር"** ብለው ስለጻፉ ፕሬዚዳንቱ ምን ዓይነት መልስ እንደሰጡዎት አላነበቡምን? እርግጠኛ ነኝ አንብበዋል፤ ግን **ውሸትን** እንጀራው ለደረገ ሰው ዛሬም ተዋረዳ ነገ ከውሸት አይርቅም፡፡ አቶ ሙሉጌታ የሚበሉት ምግብ የሚጣፍጣቸው በጨው ሳይሆን በየጊዜው የብዕር ስማቸውን እየቀያየሩ በውሸት ቅመም እየጠቀለሉ ሲውጡ ብቻ ነው፡፡ ይህ አጉል በሽታ ዛሬም በአሜሪካ አገር እየኖሩ አልለቀቃቸውም፤በመሆኑም፤ነው በማንኛውም ዓይነት መጽሐፍት ውስጥ ተጠቅሶ የማይታወቀውን **"ምኒልክ ዘወትር ምሳና እራት ሲበሉ አብሮአቸው ማዕድ የሚቀርቡ (ሁልጊዜ) ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ፤ ደጃዝማች ወልደሚካኤል ጉዲሳ፤(የአጤ ኃይለሥላሴ አያት) ፊታውራሪ ቱሉ፤ አፈንጉሥ በዳኔና ብላታ አቲካም "** ነበሩ በማለት ያለ **አቲካም** በስተቀር ሌሎችን በሙሉ ኦሮሞ አድርገው ያቀረቡአቸው፡፡ በጣም የሚገርመው ደግሞ ከፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ ጋር በመተባበር **አረመኔ፤ አውዳሚ፤**ወዘተ..ብለው በጅምላ ሲሰድቡት የነበረውን ሕዝብ ወዲያው ደግሞ ከምኒልክ ጋር ማዕድ ቀራቢና የቅርብ ሰዎች አድርገው ለማቅረብ መሞከራቸው ነው፡፡ ለመሆኑ፤ ስለምን እንደምትጽፉ እያስተዋላችሁ ይሆን? እውነት በምኒልክ ዙሪያ በወቅቱ **"ከሰሜን ሸዋ መኳንንት"** በላይ ኦሮሞዎች ቅርበት ነበራቸው? ምኒልክ እኮ በዚያን ጊዜ **"ሕዝቦቼ"** ይሉ የነበሩት **"ክርስቲያኑን የሰሜን ሸዋ መኳንንት"** እንደነበረ በብዙ መጽሐፍት ላይ ተጽፎ ይገኛል፡፡ ስለዚህ፤ ከምኒልክ ጋር ማዕድ ቀራቢና የቅርብ ሰዎች ነበሩ የተባሉት አቀራረቦች በሙሉ መረጃ አልባና የራስዎ የግል ፈጠራዎች ናቸው፡፡ በተጨማሪም፤ **"ዘወትር፤ ሁልጊዜ"** እያሉ ነገሮችን በማዳነቅ ያቀረቡአቸው ቃላቶች ምንም ዓይነት እርባና የሌላቸው ተረቶች ብቻ መሆናቸውን ቢገነዘቡ ጥሩ ነው፡፡ በአጠቃላይ የዚህን ዓይነት ተራና አሳፋሪ አስተሳሰብ ይዘው **"የፖለቲካ ተንታኝ ነኝ" ማለትዎም ግን ምን ያህል ትልቅ ወንጀል እንደሆነ ሊያውቁት ይገባል፡፡** ለማንኛውም ጥፋቱ የእርስዎ ብቻ ሳይሆን የሌለዎትን ስያሜና የጀርባ ታሪክዎን ሳይመረምሩ ለሕዝብ ያቀረቡዎት የቴሌቪዥን ጣቢያው ሠራተኞች ናቸው፡፡ እነርሱም ቢሆኑ በጊዜው ሂደት እውነታውን ይረዱታል ተብሎ ይታመናል፡፡

አቶ ሙሉጌታ ሉሌ ኢህአዴግን ለመውቀስ ብለው **"የአገር መሬት የቸበቸበ መሪ ታይቶ ተሰምቶ አይታወቅም፤በውጪ በባንክ ሚስጥር የተቀመጠውን የገንዘብ ቁልፍ መለስ ለሚስቱ ካልሰጣት እሱም በሞቱ ከስሮአል"** እያሉ ከአንዱ ርእስ ወደሌላ ርእስ እየዘለሉና ያልተጨበጠ ድርሰት እየጻፉ ገጽ ለመሙላት ሲቸገሩ ይታያሉ፡፡ ታሪክ መረጃ ይፈልጋል፤ ከተረትም የሚለይበት አንዱ ይህ ባሕሪው ነው፡፡ እርስዎ ግን ያለመረጃ ኢህአዴግ **"አገር ሸጠ"** ለማለት እየዳዳዎት ነው:: ዓለም ግን የሚያውቀው የንጉሠ ነገሥት ምኒልክ ጂቡትንና ኤርትራን መሸጣቸውን ነው፡፡ እርስዎ ባለማወቅዎ አልደነቅም፡፡ ከሞያሌ አንስቶ ወደ ኬኒያ 500 ኪሎ ሜትር ላይ የሚኖሩትን የቦረና ኦሮሞዎች ወደ ኬንያ ግዛት እንዲካለሉ ከእንግሊዝ መንግሥት ጋር የተስማሙት አጼ ምኒልክ ናቸው፡፡ እርስዎ እንደማያውቁ ለመምሰል ቢሞክሩም ዓለም ግን ያውቃል፡፡ በውጪ አገር በሚስጥር ባንክ ገንዘብ አስቀምጠዋል በማለት ለህሜት ከሚቸኩሉ በደርግ ጊዜ **በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ** የየእለቱ ርዕስዎ የነበረውን የጃንሆይን በውጭ አገር ገንዘብ ማስቀመጥ ጉዳይ ለምን ረሱት? እርስዎ ከአገር ቢወጡ ጋዜጦቹኮ እዚሁ ኢትዮጵያ ውስጥ ስለሆኑ አይቶ መፍረድ ይቻላል፡፡ ሌላስ፤አገር ከመሸጥ በላይ ሕዝባቸውን እየሸጡ ጥይትና ጠመንጃ ሲገዙ የነበሩትን መሪ ስም ለምን አልጠቀሱም?

ምኒልክ ክርስቲያን ስለነበሩ በወረራው ወቅት እጅና ጡት አልቆረጡም፤የምኒልክ አጎት ራስ ዳርጌ እጅግ ሃይማኖተኛ ሰው ስለነበሩ እንደዚህ ዓይነት ድርጊት ለመፈጸም ባህርያቸው የማይፈቅድላቸው ሰው ነበሩ፤ ስለዚህ ጡትና እጅ አልቆረጡም እያሉ ናቸው፡፡ ከዚህ በላይ ጉዳዩ የተለመደው የተረት ጨዋታ እንጂ የታሪክ ጉዳይ ስለአልሆነ ብዙም አያስጨንቅም፡፡ ለመሆኑ፤እነዚህ ጻድቃን የሆኑ ሰዎች ምን ሊያደርጉ ወደ አርሲ እንደሄዱ ለምን አላብራሩም ነበር? ይህ አባባላችሁ እውነት ከሆነ ለምንድነው መረጃ ያልጠቀሳችሁት? አጼ ዮሐንስና ንጉሥ ምኒልክ **ከቦሩ ሜዳ** ስምምነት በኋላ የወሰዱት የግድያ እርምጃዎች ምን ተብሎ ሊመዘገብ ይችላል? ክርስትያኖች ሕዝብ የማይገድሉና ግፍ የማይፈጽሙ ከሆነ የክርስትና እምነት እንዴት ሊስፋፋ እንደቻለ ለምን አልተብራራም ነበር? **ደቂቀ እስጢፋኖስ** በማለት ፕሮፌሰር ተብየው ጌታቸው ኃይሌ በጻፉት መጽሐፍ ላይ "**አጼ ዘረ ያዕቆብ በአስተምሮ በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት መምህራን ለየት ያለ አቋም የያዙትን ሰዎች አስገደለ፤ አገዳደሉም አፍንጫቸውን፤ ከንፈራቸውን፤ ምላሳቸውን እንዲቆረጥ ከተደረገ በኋላ በአደባባይ ለሕዝብ ማስደንገጫ ተብሎ ከአንገት በታች ተቀብረው የፈረስ አጎዳ በላያቸው ላይ በመንዳት ነበር**" በማለት በመጽሐፋቸው ውስጥ የጠቀሱትን አላነበቡትምን? ግፎችን በደረጃ ለማስቀመጥ እጅግ በጣም ከባድ ቢሆንም፤ **ከአኖሌ** ግፎች ጋር ቢወዳደሩ አይበልጡምን? እነዚህን ድርጊቶች የፈጸሙት ክርስትያኑና የአገሪቷ መሪ አልነበሩምን?

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ በመጽሐፋቸው ውስጥ እ.ኢ.አ በ1769ዓ. ም. ክርስቲያኑ ራስ ሚካኤል ስሁል ንጉሥ ኢዮአስን በሻሽ አንቀው ገደሉ፤የዳሞቱ ገዥ የነበሩትን የፋሲል ወታደር የራስ ሚካኤል ስሁል ወታደሮች ገድለው፤ቆዳቸውን ገፈውና እንደ ስልቻ ሰፍተው ገለባ ሞሉ፤ደጃች ካሣ (በኋላ አጼ ዮሐንስ) የእህታቸው ባል የነበሩትን አጼ ተክለጊዮርስን በ1863ዓ.ም.አድዋ ካለው ሜዳ ላይ አሸንፈው ሁለቱንም ዓይናቸውን አውጥተው፤ አባ ሰላማ በሚባለው ተራራ ላይ አሰሩአቸው በማለት የጠቀሱአቸው ሁለቱም መሪዎችና ጦራቸው ክርስትያኖች አልነበሩምን? አጼ ቴዎድሮስና አጼ ዮሐንስ በወሎ ሕዝብ ላይ የፈጸሙአቸው ግፎች በብዙ መጻሐፍት ላይ ተጽፎ ለመካድ በማይቻል ሁኔታ ቁልጭ ብሎ ተቀምጧል፡፡ በተለይም አጼ ቴዎድሮስ የእስረኞቻቸውን እጅና እግር ከቆረጡ በኋላ ከመቅደላ ተራራ ላይ ከነሕይወታቸው ቁልቁል ወደ ገደል በመወርወር በየእለቱ ይፈጽሙ የነበሩት ግፎች ምን ጊዜም የሚረሱ አይደለም፡፡ ታዲያስ፤ፕሮፌሰር ጌታቸው፤ ሌሎቹን ተጨማሪ ማስረጃዎች ትተን እነዚህን ድርጊቶች ብቻ ብንወስድ አባባልዎን ውድቅ አያደርጉትምን?

ምኒልክ የኦሮሚያንና የደቡብ ሕዝቦችን አገር ወረዋል፤ሕዝቦችን ገድለዋል፤የጦር መሪዎቻቸው ራስ ዳርጌና አዛዥ ወልደ ገብርኤል የአርሲንና የሐረር ኢቱ ኦሮሞዎችን የወንዶችን ቀኝ እጅ፤የሴቶችን ቀኝ ጡት በመቁረጥ ኢሰበኣዊ ድርጊት ፈጽመዋል፡፡ ለዚህም ማስታወሻ በአሁኑ ጊዜ አርሲ ውስጥ **አኖሌ** በሚባል ቦታ ትልቅ ሀውልት ተሰርቶ ተጠናቋል፡ ተመርቋልም፡፡ይህንን ለማድረግ የኦሮሞ ሕዝብ የናንተን እውቅና አይፈልግም፤የሚካሄዱትንም ተቃውሞች እንደ አመጣጣቸው ያስተናግዳል፡፡ አረ ለመሆኑ፤ የኦሮሞን ሕዝብ ሲጨፈጭፉ ለነበሩት መሪ ሀውልት ከቆመ ለተጨፈጨፉት ወገኖች ደግሞ እንዲሁ ሀውልት ቢቆምላቸው ምንድነው ስሕተቱ? ለምንስ ትናደዳላችሁ? ጨፍጫፊው በጀግንነቱ ፤ ተጨፍጫፊው ደግሞ በደካማነቱ ይታወሳል ማለት ነው፡፡ ሁለቱም ለመጪው ትውልድ መተላለፍ ያለባቸው የአገሪቷ ቅርሶች መሆናቸውን መዘንጋት የለብንም፡፡ ይህ ደግሞ የሕዝብ ውሳኔና ፍላጎት ስለሆነ ሊከበር ይገባል፡፡የኦሮሞ ሕዝብ ያልተደረገውንና ያልተፈጸመውን ድርጊት ተፈጽሟል ብሎ ለምን ሀውልት ይሠራል? ማንንስ ለማስታወስ ብሎ ነው? ምንስ ግዴታ አለበት? ድርጊቱ ስለአመንክ የሚሆን፤ስለካድክ የሚቀር ጉዳይ ሳይሆን ሊፋቅ የማይችል የታሪክ እውነታ ስለሆነ ብቻ መሆኑን ከልብ ልንገነዘብ ይገባል፡፡

ስለ**አኖሌ** ታሪክ ጊዜውና ሁኔታው የፈቀደላቸው ሰዎች በቂ መረጃዎችን ተንተርሰው በብዛት ጽፈዋል፤አንዳንዶቹ "**ምንም አላነበብንም**" ስለአሉ ታሪኩ አልተጻፋም ማለት አይቻልም፡፡ ከዚያም በላይ ደግሞ በሕይወት የሌሉ ወላጆቻቸው ላይ ይህ አሳዛኝ አደጋ የደረሰባቸው ልጆቻቸው ዛሬ በሕይወት የሚገኙ አሉ፡፡ ስለዚህ ፤ እውነተኛዎቹ ተመራማሪዎች እነዚህንና ሌሎቹንም መረጃዎች በመጨመር የድርጊቶቹን መፈጸምና አለመፈጸም ሊነግሩን ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ምንም ዓይነት ሰነዶችን ሳይመረምሩ ፤ በሕይወት ካሉት ነዋሪዎች መረጃ ሳይሰበስቡ እንዲሁ "**ያልተደረገ ሥራ ነው፤ እኔ የአኖሌን ሀውልት መቆም አልደግፍም** " በማለት ብቻ ውጤት መምጣት ይቻላልን? ለመሆኑ፤ ስለኦሮሞ ሕዝብ ጉዳይ (ግዴታ ካልሆነባችሁ በስተቀር) ከስሙ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ የደገፋችሁት ነገር ምን ምን እንደሆነ ቢፈለግ ይገኝ ይሆን ? "**የኦሮሞ ሕዝብ፤ መጤ ነው፤ሃይማኖት የለውም አረመኔ ነው በውኃና በተራራ ያመልካል፤ገዳ የማፈያ ሥርዓት ነው፤ በቁቤ መጠቀሙ ትክክል አይደለም፤ወዘተ..**" ሲባሉ የነበሩት ስድቦችና ተረቶች አሁንም እንዲቀጥል የሚፈልጉ ግለሰቦች መኖራቸው ምንም የሚደንቅ ነገር የለውም፡፡ የሚያሳዝነው ግን ለምን ኦሮሞ ሕዝብ ላይ ብቻ ? የሚለው ነው፡፡ ሌላው ቀርቶ የአገሪቷ ሕገ መንግሥት ላይ ለሁሉም የአገሪቷ ብሔር፤ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ይጠቅማል ተብሎ የጸደቀውን **አንቀጽ 39** ላይ "**ከኦሮሞ ሕዝብ በስተቀር**" የሚል ሀረግ ቢጨመርበት ሁላችሁም እንደምትደግፉት

እርግጠኛ ነኝ፡፡ የተቃወማችሁትና የከከናችሁ የኦሮሞን ሕዝብ ስለጨመረ ብቻ ለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም፡፡ የሚካሄደው አጉል ተቃውሞ በምንም ዓይነት ታሪካዊ እውነታውን ሊያፋልስ እንደማይችል፤ ዘመቻው የኦሮሞን ሕዝብ እንዲነቃ የሚያደርግ እንጂ ወደኋላ የሚመልሰው እንዳልሆነ ሊታውቁት ይገባል፡፡ ጉዳዩ **የወጋ ቢረሳ የተወጋ አይረሳም** እንደሚባለው ሆኖ ነው እንጂ በእውነት የድርጊቱን ሂደት ሳታውቁት ቀርታችሁ እንዳልሆነ ግልጽ ነው፡፡ የተፈሩትና ለዘመናት እንደታሪክ እየተቆጠሩ የመጡት ተረቶች በግድ ይፈርሳሉ እንጂ ተረቶቻችሁ እንዳይፈርሱ ለመሸፋፋን የኦሮሞ ሕዝብ እውነተኛው ታሪኩ ተደምስሶ እንዳለፉት ዘመናት ታሪክ አልባ እየተባለ እንደማይኖር ሊሰመርበት ይገባል፡፡

ሌላው በጣም የሚያሳዝነው ደግሞ መረጃ-አልባ ተረታችሁ ነው፡፡ በአንድ በኩል ክርስቲያኖች እንደዚህ ያለውን ግፎች አይፈጽሙም፤ እንደዚህ ያሉት ግፎች የሚፈጸሙት በአረመኔዎች ነው፤ካላችሁ በኋላ በግፉ ፈጻሚነት የተጠቀሱትን የጦር መሪዎችን ትታችሁ ወደ አልተባሉት ራስ ጎበና ትሄዳላችሁ፡፡ ራስ ጎበና ከክርስቲያኑ በላይ ክርስትያን በመሆን ቀደም ሲል በተስማሙበት መሠረት ቃላቸውንና እምነታቸውን ጠብቀው ምኒልክን በመርዳት ለከፍተኛ ደረጃ ያደረሱና በኦሮሞ ክልል ወረራ ላይ በግንባር ቀደምትነት የተሰለፉ የምኒልክ ቀኝ እጅና ጦር መሪ እንደነበሩ ዓለም ያውቃል፡፡ ነገር ግን የእሳቸውን ውለታ ንጉሥ ምኒልክም ከደው እንደሞቱ ሁሉ እናንተም ዛሬ እሳቸውን ወደ **አረመኔነት** ለመውሰድ ብትሞክሩም ምንም አያስገርምም፡፡ ለማንኛውም ወደ ራስ ጎበና ለመንተት የምትሞክሩትን ተንኮል ብትተውት ይሻላል፡፡ የራስ ጎበና ጦር የኦሮሚያን ክልል መውረሩ ሊካድ አይችልም፤ ነገር ግን እናንተ እንደአቀረባችሁት ሳይሆን ጦራቸው በጡትና በእጅ ቆረጣ ድርጊት ላይ እንዳልተሰማራ የታሪክ ምሁራን የሚመሰክሩት ሀቅ ነው፡፡ የራስ ዳርጌ ጦር ግን በጦርነት የአርሲን ሕዝብ ድል ካደረገ በኋላ ብዙ ወራት ቆይቶ ሕዝቡን በመሰብሰብ ወንዶቹን የቀኝ እጅ፤ሴቶቹን የቀኝ ጡት መቁረጡ የተረጋገጠ የታሪክ ሀቅ ነው፡፡ በመሆኑም፤ በሕይወት ዘመናቸው በሙሉ የጡት ቆረጣ እለት እንደ ድል በዓል ተቆጥሮ በየዓመቱ ይከበር እንደነበረ፤ከእሳቸውም ሞት በኋላ እስከ ኃይለሥላሴ ዘመን መጨረሻ ድረስ በዘመዶቻቸው ቀጥለው ሲከበር እንደቆየ ሊዋሽ የማይቻል የቅርብ ጊዜ ትውስታ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡

አቶ ሙሉጌታ አጼ ምኒልክ ሁሉንም **"አበሻ"** በእኩልነት መርተዋል፤ ኢትዮጵያ እንደ ምኒልክ ያለ መሪ ታድላ አታውቅም ይሉናል፡፡ሌሎችም የእርስዎን አመለካከት የሚጋሩ (የአጼ ምኒልክ የአንድነት ጥረት ለምን ከመጥፎ ጎኑ ብቻ ይተነተናል? እሳቸው ባይደርሱ ኖሮ ቅኝ ገዥዎች ይወሩ አልነበረምን? ታሪክ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ዓይነት በመረጥነው አልተወከልንም የሚባል ዓይነት ሊሆን ይችላልን? ወዘተ…) ሰዎች እንዳሉ አለፍ አለፍ ተብሎ በየጋዜጦቹ ላይ ይታያሉ፡፡ነገር ግን ሁላችንም ማወቅ ያለብን ምኒልክ የፊውዳል ሥርዓት መሥራች መሆናቸውን፡፡ ከቁርጥ ግብር ማስከፈል ጀምሮ እስከ ገባር ሥርዓት ድረስ የመሠረቱት አጼ ምኒልክ ናቸው፡፡ ይህ ደግሞ ግማሹ ባለርስት ግማሹ ጪሰኛ፤ግማሹ ጌታ፤ ግማሹ ባሪያ የሆነበት ሥርዓት ስለነበረ በምንም ዓይነት የእኩልነት ምልክት ሊኖረው የማይችል ሥርዓት ነበር፡፡ ይህንን አስተዳደር ሲመሩ የቆዩት ንጉሠ ነገሥት ምኒልክ እንዴት የአበሻን (ሁሉንም የኢትዮጵያ ሕዝብ ለማለት ከሆነ) ሕዝብ በእኩልነት አስተዳድረዋል ይባላል? ይህ በፍጹም ሀሰት ነው፡፡ ነገሥታቶችም ሆኑ ሌሎች መሪዎች በአስተዳደር ዘመናቸው ጥሩና መጥፎ ሥራዎችን ሠርተው እንደሚያልፉ ይታወቃል፡፡ ሁሉንም በየፈርጁ የማቅረቡ ሥራ ደግሞ የታሪክ ጸሐፊዎች ኃላፊነት ነው፡፡በዚህ መሠረት የምኒልክ በጎ ሥራዎች ብቻ ለምን አይጠቀሱም? የሚሉ ሰዎች ምን ያህል ስሕተት ላይ እንደወደቁ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የአጼ ምኒልክን ደግነት ብቻ የሚገለጽበት የመዋዕለ ዜና አቅራቢዎች ዘመን ማለፉን ተወደደም ተጠላ ልናምን ይገባል፡፡ ከሰሜን ኢትዮጵያ በማምጣት ያሰፈሩአቸውና ጌታ ያደረጉአቸው ሕዝብ **እምዬ ምኒልክ** በማለት ቢያስታውሱአቸው መብታቸው ነው፡፡ ነገር ግን በምኒልክና ከዚያም በኋላ እስከ ደርግ ሥርዓት መጀመሪያ ድረስ ነጻነታቸውን አጥተው ለባርነት ከመዳረጋቸውም በላይ ሰበዓዊ መብታቸው ተረግጦ እንደእቃ እየተሸጠ የጦር መሣሪያ መግዣ ሆኖ የነበረው ሕዝብ ደግሞ በወራሪነትና በነፍጠኛ ሥርዓት ፈጠሪነት ያስታውሱአቸዋል፡፡ይህ ሊካድ የማይችል የታሪክ ሀቅ ነው፡፡በዚህም የተነሳ ይህ ሕዝብ የአውሮፓ ቅኝ ገዥዎች ከምኒልክ ቀድመው ቢወሩት ኖሮ ከምኒልክ ሥርዓት የተሻለ ሁኔታ ይፈጠር ነበር ብሎ ያምናል እንጂ ከዚያ የበለጠ ግፍ ሊፈጸምብን ይችል ነበር የሚል እምነት የለውም፤ ሊኖረውም አይችልም፡፡ አለቃ አጽሜ የሚከተሉትን ምስክርነት ይሰጣሉ፡፡

በዳግማዊ ምኒልክ ዘመን ጋላ/ኦሮሞ ሁሉ ተገዛ ባማራ ሕግና ሥርዓት ሄደ፤

ካህናቱ ግን አንድ ኦሮሞ አስተምረው አላጠመቁም፤ይልቅስ ተፈተኛው ቂም

የበለጠ ቂም በልቡ አኑረውበት፤ መሬቱን በቀላድ ወሰዱበት፤እንድ ቀላድ የቄስና

የቀላድ አወዳሽ እያሉ በዚሁ ስብከት ንጉሡን አሳመኑ፤ስለመንግሥት ያሰቡ

መስለው ለንግሡም አንድ ቀላድ፤ለገባር አንድ ቀላድ፤ለወታደር አንድ

ቀላድ፤....መሬቱን ተካፍለው ኦሮሞውን እንደ ባሪያ አድርገው ይገዙታል እንጂ

የክርስቶስን መንገድ አላሳዩትም፤ እነሱም አልተማሩም፤ አስተማሪም ቢመጣ

ይከለክላሉ፡

ታዲያ፤ የአውሮፓ ቅኝ ገዥዎች ከዚህ በላይ ምን ያደርጉአቸው ነበር?

ሌላው በጣም የሚገርመው እስከ ዛሬ ድረስ ተያይዞ የመጣውን የነገሥታቶች ታሪክ ተብዬ ተረቶችን አሁንም እንደ ታሪክ አድርገን እንድንወስድ የሚገፋፉን ሰዎች መኖራቸው ነው፡፡ ለዚህም መነሻ የሆነኝ ሰሞኑን በመንግሥት ደረጃ እስከዛሬ ድረስ የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ ሲባል የነበረውን ተረቶቹ ፈርሰው የሕዝብ ታሪክ የሚጻፍበት መንገድ ለመፈለግ እርምጃ ለመውሰድ በተነሳበት ሰዓት የቱን አፍርሶ የቱን ለመገንባት ነው? ማንን ጠቅሞ ማንን ለመጉዳት ነው? እየተባለ በየጋዜጦቹ ላይ ፉከራ ዓይነት ጽሑፎች ለንባብ መብቃታቸው ነው፡፡ ፕሮፌሰር ታደሰ ታምራት **ተረትና ታሪክ በኢትዮጵያ** በተሰኘው ጥናታቸው **"አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ምሁሩም ሳይቀር ስለአገሩ ያለው መሠረታዊ አስተያየት ከየተረቱና ከየአፈ-ታሪኩ ያላለፈ ነው"** የሚለውን ጥቅስ የሚያቀርብ ጸሐፊ ወረድ ብሎ ታሪክን **"እንደ ፌዴሬሽን ምክር ቤት በመረጥነው አልተወከልንም እንደማይባል"** አድርጎ ማቅረቡ ምን ያህል የታሪክን ምንነት እንዳልተረዳን ያሳያል፡፡ በገዥው መደቦች በኩል ሕዝቡ እንዲያውቀው የተፈቀደለት ተረቱንና አፈ-ታሪኩን ብቻ ነው እያሉ እየነገሩን ታሪክን ማሻሻል አይቻልም ማለት ምን ማለት ነው? እያንዳንዱ ሕዝብ እንዲታወቅለትና ለሚቀጥለው ትውልድ እንዲተላለፍለት ይዞት የመጣ ሃይማኖት፤ባህልና ወግ አለው፡፡እነዚህ ሁሉ ተመዝግበው በታሪክነት እንዲተላለፉለት ይፈልጋል፡፡ሕዝቦች በጋራ የተሳተፉባቸው የአድዋና የማይጨው ጦርነቶች ብቻ ለጋራ ታሪክነት ይበቃል ሳይሆን የኅብረተሰቡን ፖሎቲካዊ፤ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጉዳዮችን የሚመለከቱ ሁሉ ሊመዘገቡ ይገባል፡፡ በዚህ ዓይነት መልክ ተጽፈው ያልመጡ ሁሉ ተረቶች ስለሆኑ በተረትነታቸው ይተላለፋሉ እንጂ ስለቆዩ ብቻ ወደ ታሪክነት አይለወጡም፡፡ በሌላም በኩል ቀደም ብለው ያልተጻፉት ዛሬ ተጽፈው ታሪክ ሊሆኑ አይችሉም ማለት አይደለም፡፡ስለዚህ፤ ታሪክ ተረት ሆነ ሳይሆን የተረት ታሪክነት ተሰርዞ በተረትነቱ ታወቀ ማለት ነው፡፡ ነገር ግን ዋናው ጉዳይና መገንዘብ ያለብን ታሪክ የሚዘጋጀው በማንኛውም ሰው መሆኑን ነው፡፡ ጸሐፊው በተጽእኖ ምክንያት፤እውነተኛውን መረጃ ከማጣት የተነሳ ፤ወይም ከአተረጓጓም ችሎታ ማነስ አንጻር ወዘተ... ብዙ ነገሮችን ሊሳሳት ይችላል፡፡እነዚህን ሁሉ አርሞ ለሚቀጥለው ትውልድ ሊተላላፉ የሚገባቸውን በካሪኩለም ውስጥ አስገብቶ የማስተማሩ ጉዳይ የመንግሥት ኃላፊነት ነው እንጂ "**በፋክት መጽሔቱ** "ላይ እንደተጠቀሰው **"ከግል ጥላ ጋር መነታሪክ"** ሊሆን አይችልም፡፡ ታሪክ መረጃን ተንተርሶ ይጻፋል፤ በተጻፋውም ላይ የበለጠና አሳማኝ መረጃ ሲቀርብበት ይፈርሳል፡፡

አጼ ምኒልክ በመጥፎ ጎን ብቻ ሳይሆን በጥሩ ጥሩ ጎኖችም ይነሳሉ፡፡ በዓለም ሕዝብ ዘንድ የሚታወቁት በአድዋ ጦርነት ድል አድራጊነት ነው፡፡ በማስተባበር ችሎታቸውና ዘመናዊ ጦር መሣሪያ ከታጠቀው የነጭ ወራሪ ጋር ጦርነት ገጥመው ድል በማድረግ ገናናዎቹን የአውሮፓ አገሮች የሀፍረት ማቅ ያለበሱ በዚህ ረገድ እውነተኛ የአፍሪካ ልጅ ናቸው፡፡ የምኒልክ ታሪክ ከአድዋ ጦርነትና የጦርነቱ ውጤት ለዓለም ጥቁር ሕዝቦች ካበረከተው አስተዋጽዖ አንጻር እስከ አሁን ድረስ ብዙ እንዳልተጻፈላቸው ይታወቃል፡፡ሆኖም ታሪክ በአድዋ ጀግንነታቸው እያስታወሳቸው ነው፡፡

አቶ ሙሉጌታ ሉሌ ከኦሮሞዎች ጋር ለመወዳጀት ሲፈልጉ ብዙ መንገዶችን  ይጠቀማሉ፡፡ አንዱ ዘዴአቸው ከሚጠረጠሩትና እንዲከታተሉአቸው ከተነገሩአቸው የኦሮሞ ምሁር ወይም ነጋዴ እንደምንም ብለው ለተወሰኑ ጊዜያት ጓደኛ ያደርጋሉ፤ መረጃ ይሰበስባሉ፤ትንሽ ቆይተው ያሳስራሉ፤ ወይም ያስገድላሉ፡፡ የዚህ ዓይነት አደጋ ሰለባ የሆኑት ብዙዎች ቢሆኑም እስቲ የብርጋዴር ጄኔራል ታደሰ ብሩን ጉዳይ እንመልከት፡፡ በመጀመሪያ ከአንድ ጋዜጠኛ ጓደኛቸው ጋር ሆነው የባለቤታቸውን **ብሔር** እንደ ዝምድና በመጠቀም **"አማቻችን ቤት ነው"** እያሉ ባስፈለጋቸው ጊዜ ዘመድ መስለው ቤታቸው በመሄድ እየበሉና እየጠጡ የወቅቱን የትግል ወቅት ለማጨናገፍ የሚያስፈልጋቸውን የውሸት

ዜናዎችን እየሰበሰቡ በመንግሥት ዘንድ ታማኝነታቸውንና አገር ወዳድነታቸውን እያረጋገጡ፤ ሌሎችንም ጥቅማ ጥቅሞች ሲያገኙ ከቆዩ በኋላ ላይ ብ/ጄኔራል ታደሰ ብሩ ሊታሰሩ አካባቢ ወደ ቤታቸው መመላለሱን አቋረጡ፤ ስልክ መደወሉንም ተውት፤ ሲደወልላቸውም አያነሱም ነበር፡፡ ብ/ጄኔራል ታደሰ ብሩም እንደታሰሩ የቤተሰብ አባላት በየአቅጣጫው እነዚያን **"አማቾች ነን"** ሲሉ የነበሩትን ማፈላለግ ቢጀምሩም በፍጹም ግን ሊገኙአቸው አልቻሉም፡፡ በእስራቱም ዘመን አንድም ቀን ጄኔራሉንም ሆነ ቤተሰባቸውን ጠይቀው አያውቁም፡፡ ከእስር ቤት ከተፈቱም በኋላ **አደገኛ ሰው ናቸው፤ መፈታት አልነበረባቸውም፤** በማለት ለደርግ ባለሥልጣናት በየጊዜው ያልሆኑ ሪፖርቶችን በማስተላለፍ በመጨረሻም ለሞት ከአበቁአቸው ሰዎች መካከል በዋናነት ደረጃ ሁለቱ የወቅቱ ጋዜጠኞችና የደህንነት ሠራተኞች እንደነበሩ የጄኔራሉ የቅርብ ሰዎች ዛሬም ያስረዳሉ፤ድርጊቱንም ከከባድ ሀዘን ጋር ያስታውሳሉ፤ በአደባባይም ምስክርነታቸውን የሚሰጡበት ጊዜ እሩቅ እንደማይሆንም ያላቸውን እምነት ይገልጻሉ፡

አቶ ሙሉጌታ በቅርቡም የጦቢያ መጽሔት አዘጋጅ በነበሩ ጊዜ አንዱን የኦሮሞ ምሁር ጊዜያዊ ወዳጅ፤ሌላውን ጠላት በማድረግ እንዴት እርስ በርስ ሲያባሉ እንደነበረ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው፡፡ በደራሲው በዓሉ ግርማም ሞትም ላይ ምን ዓይነት ሚና እንደነበራቸው በብዙ መጻሐፍት ተጽፎ ይገኛል፡፡

አቶ ሙሉጌታና ፕሮፌሰር ጌታቸው በኢንተርኔትና በሎሚ መጽሔት ያቀረቡት ጽሑፎች ርዕሳቸውና የገጽ ብዛታቸው ብቻ ይለያያል እንጂ በይዘታቸው አንድ ናቸው፡፡ ሁለቱም በሸዋው ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ዘመን **አምስት ሚሊዮን ኦሮሞ** አለቀ የሚለውን መረጃ ወደ ምኒልክ ዘመን ወስደው በማሸፍ መልክ ተችተዋል፤የሚቻላቸውንም ተረቶች አቅርበው እውነታውን ለማጣጣል ሞክረዋል፡፡ የታሪክ ሀቁ ግን የፈለቀው እ.አ.አ በ1834ዓ ም ከንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ጋር የእንግሊዝን መንግሥት በመወከል የንግድ ስምምነት ከፈረሙትና ለመጀመሪያ ጊዜ የመድፍ ስጦታ ከሰጡአቸው፤ እንዲሁም በየወረራው ቦታዎች ሁሉ ከንጉሡ ጋር በመሄድ ድርጊቱን በዓይናቸው ሲመለከቱ ከነበሩት ከእንግሊዛዊው **ካፒቴን ኮርንዎሊስ ሃሪስ**(Harris: Vol: III: 38-9) መሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡ እሳቸውም ስለሁኔታው ሲገልጹ፡ **"ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ በ30 ዓመታት ሥልጣን ዘመናቸው አንዴም ሳይቋረጥ በየዓመቱ ሶስት ጊዜ ከአንኮበር ቤተ መንግሥታቸው እየተነሱ በአካባቢያቸው በሚኖሩት ኦሮሞ ሕዝብ ላይ ዘመቻ ያካሂዱ ነበር"** በማለት ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል፡፡ ይህ እልቂት ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ የእህልና የሳር አጨዳ አዝመራን እየጠበቁ በየጊዜው ከማሳና ከአውድማ ላይ በመዝረፍና በማቃጠል እንዲሁም ከብቶቻቸውን በመቀማት በረሃብ አለንጋ የፈጁአቸውንና በወረራው ላይ የሞቱትን ሁሉ እንደሚጨምር በየጽሑፉ በደንብ ተብራርቷል፡፡ ቀደም ሲል **ከአስር ሚሊዮን** በላይ የነበረው የኦሮሞ ሕዝብ በንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ዘመን ወደ አምስት ሚሊዮን አሽቆለቆለ ያሉት ከዚህ የተነሰ ለመሆኑ ልንጠራጠር አይገባም፡፡ በአጼ ምኒልክ ዘመን ያለቁት ኦሮሞዎች **አምስት ሚሊዮን** ብቻ ነበሩ ብሎ የሚገምት ሰው ይኖራል ተብሎ አይታሰብም፡፡ እናንተም ብትሆኑ እንደዚህ ዓይነት ውርደት ውስጥ ትገባላችሁ ተብሎ አይታመንም፡፡ ለመሆኑ፤እነ አለቃ አጽሜ ሁልጊዜ ነገሥታቶቹ ገደሉ፤አሸነፉ፤የጠላት ሬሣ እንደ ድንጋይ ከመሩ እያሉ ጀግንነታቸውን ይገልጹ አልነበረምን? ያንን ሁሉ መረጃ ብንወስድ ያለቀው ሕዝብ ቁጥር ስንት የሚሆን ይመስላችኋል? ለማንኛውም በምኒልክ አስተዳደር ዘመን ያለቁት የሸዋ ቱለማና መጫ፤ የወሎ፤የአርሲ፤ የሀረርጌ ፤የባሌ፤የሐረር፤ ኢሉአባቦር፤የወለጋ ወዘተ..ሕዝብ ቁጥር እጅግ በጣም ብዙና ጊዜውን ጠብቆ የሚገለጽ ስለሆነ ለአሁኑ ግን አምስት ሚሊዮኑ የንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ዘመን ብቻ እንደነበረ ልታወቅ ይገባል፡፡

በምኒልክ ዘመን ብዙ አሰቃቂ ድርጊቶች በሕዝቦች ላይ እንደደረሱ በብዙ ጸሐፊዎች የተገለጹ ስለሆኑ መቀበሉ የግድ ይሆናል፡፡ለምሳሌ፡ ላንጌ፡ደብሊዩ (Lange, W. 1979. Domination and Resistance: Narrative songs of the Kaffa Highlands…) የተባሉት ደራሲ ስለ **ከፋ ሕዝብ** በምኒልክ ጦር መወረር ሲጽፉ፡ **"የምኒልክ ቅኝ ግዛት ወረራ የከፋን ነዋሪ ሕዝብ ሁለት ሶስተኛውን በመፍጀቱ ብቻ የሚታወስ ሳይሆን፤ በተረፈውም ሕዝብ ላይ ትቶት ባለፈው ዘግናኝ የሆነ የህሊና ቁስል ጭምር ነው" ብለዋል፡፡**

አቶ ሙሉጌታና ፕሮፌሰር ጌታቸው የጡትና የእጅ ቆረጣ ድርጊት የአረመኔዎች ሥራ ነው እያሉ ናቸው፡፡ ለመሆኑ፤ የትኛውን ሕዝብ ነው **"አረመኔ"** ለማለት የፈለጉት? በእውነቱ የትኛው ሕዝብ **"አረመኔ"** እንደሆነ ሁለቱም በአሁኑ ጽሑፋቸው ላይ ግልጽ ባያደርጉትም ካለፉት የተረት ጽሑፋቸውና አሁንም ከተነሱበት ዓላማቸው አንጻር ያው የኦሮሞን ሕዝብ ለመሆኑ የአደባባይ ሚስጥር ነው፡፡ አንብቦ ለመረዳት ያለው የእውቀትና የፍላጎት ችግር ሆኖ ነው እንጂ የኦሮሞ ሕዝብ እንደዛሬ ዋቄፈታ፤ክርስቲያን፤ሙስሊም ወዘተ …እያለ በተለያዩ እምነቶች ሳይከፋፈል ሁሉም አንድ **ዋቄፈታን** ብቻ የሚከተል ሕዝብ እንደነበረ ታሪክ የሚመሰክረው ሀቅ ነው፡፡ ዋቄፈታ የጥንት ኩሽ ሕዝብ እምነት፤ የኢብራዊያን አባት ሙሴ ግብጽ በነበረበት ወቅት ሲከተለው የነበረ የአንድ አምላክ እምነት ነው፡፡ **የኢትዮጵያ**

**ቤተክርስቲያን ጥናት መጽሔት ቁጥር 2 ነሐሴ 2012** ላይ እንደ ተገለጸው **"ኦሮሞ ከጥንቱ በእግዚአብሔር ሕልውና ያምን የነበረ ብሔረሰብ እንደሆነ፤ በጥንተ ታሪኩ ከዋቃ ቶከቻ በቀር ሌላ እንደማያውቅ፤የማምለኪያ ሐውልትና ተመሳሳይ ጣዖት (የአምልኮ ምስል) እንዳልነበረው ተብራርቶ ተገልጾአል፡፡** ይህንንና የመሳሰሉትን ግልጽ መረጃዎች ሆን ብለው የማይቀበሉና እድሜያቸውን ሙሉ ከኦሮሞ ሕዝብ ትከሻ ላይ የማይወርዱ የአእምሮ በሽተኞች የተለያዩ ስሞች ሲሰጡት ኖረዋል፡፡ለመሆኑ፤ከናንተ ስድብ ለመዳን የግድ የናንተን ሃይማኖት መከተል አለበት? የኦሮሞ ሕዝብ አንድ አምላክ ብቻ ያምናል እየተባለና ዓለም እየመሰከረ፤እናንተ ግን **አረመኔ** ነው **፤ሃይማኖት የለውም** እያላችሁ የረጀ መዝሙራችሁን በመዘመር ላይ ናችሁ፡፡ ተወደደም ተጠላ ዛሬ የዋቄፈታ እምነት ተከታዮች ሕጋዊ ፈቃድ አግኝተው በመደራጀት በየአካባቢያቸው ማኅበር አቋቁመው እምነታቸውን በነጻ እያካሄዱ ናቸው፡፡ሥራችሁ ትዝብት ላይ ጠላችሁ እንጂ ሌላ ፋይዳ አላመጣም፡፡ቀደምም ሲል በአጼ ምኒልክ እና በአጼ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት የቤተ ክህነት መሪዎች ፈረንጆች አፍሪካን ለመውረር የመጡበትን ምክንያት ሕጋዊ ለማድረግ ሲጠቀሙበት የነበረውን ቃል (pagan) ተርጉመው **"አረመኔ ፤እምነት የሌላቸው"** እያሉ ሲሳደቡ ቢቆዩም፤ አንዳንድ የዋቄፈታ መሪዎች (አባ ሙዳዎች) ግን በወቅቱ በመንግሥት ዘንድ ታውቀው በሕጋዊ መንገድ ግብር ይከፍሉ እንደነበረ ዛሬ በእጃቸው የሚገኙት ደረሰኞቻቸው ቋሚ ምስክሮች ናቸው፡፡ በመሆኑም፤ ውዥንብር ነዥዎች እስከዛሬ ድረስ በኦሮሞ ሕዝብ ላይ ሲያስተላልፉ በቆዩት ተረቶች ምንም ዓይነት ፋይዳ እንዳላገኙ መገንዘብ አለባቸው፡፡ ሌላው ቢቀር እውነቶችና ተረቶች በጣም የተራራቁ መሆናቸውን በዚህ እድሜአችሁ ልያውቁት ይገባል፡፡

ሶስተኛውና አስታራቂ መስለው፤ ስለ ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ ትልቅነት እና በእውቀት፤ በምርምርና በጥናት መካን በመመስከር ከምስጋና ጋር ዝቅ ብለው እጅ በመንሳት ቡድኑን  የተቀላቀሉት **ዲ/ን ኒቆዲሞስ ዕርቅ ይሁን** ናቸው፡፡ ዲ/ን ኒቆዲሞስ፤እውነት ግን ፕሮፌሰር ተብየው ጌታቸው ኃይሌ ጥናትና ምርምር አካሂደው ያውቃሉ? ይህንን ጥያቄ የማቀርብልዎት ሙያዬ የታሪክ ተመራማሪና የአርኪዮሎጂና የቅርስ ባለሙያ ነኝ ስለአሉ ከሙያዎ አንጻር ምስክርነትዎን እንዲያረጋግጡልኝ ፈልጌ ነው፡፡ ብዙዎቻችን እንደምናውቀው እሳቸው ሲሰሩ የቆዩት ቀደም ሲል ወደ ግዕዝ ተተርጉመው የነበሩትን የሃይማኖት መጻሐፍት ወደ አማርኛ መመለስ ብቻ ነበር፡፡ ትርጉሞችን እንደ ምርምርና ጥናት አድርገው እንደማይወሰዱ ግልጽ ነው:: ከዚህ ውጭ ምን ዓይነት ምርምሮችን እንዳቀረቡ ለማወቅ በጣም እየጓጓሁ ነው፡
፡

ዲ/ን ኒቆዲሞስ፤አንድ ግለሰብ ስለአንድ ነገር ጽፎ ለሚዲያ ሲያስተላልፍ የጻፉት ነገር ለኅብረተሰቡ ምን ይጠቅማል? ወጣቱ ትውልድ ከዚህ ምን ይማራል?  የጽሑፍ ይዘት ሕዝቦች ተከባብረው በጋራ አብረው እንዲኖሩ የሚረዳ ነው? ታሪካዊ መረጃነቱስ ምን ያህል የተጠናከረ ነው? ወዘተ..ብለን የመጠየቁና የመመርመሩ ኃላፊነት የሁላችንም ቢሆንም በተለይ ግንየዚህ ዓይነት የታሪክ አደራ የተጣለበት እንደርስዎ ዓይነቶቹ **የታሪክ ተንታኞች** ናቸው ብዬ አምናለሁ፡፡ ነገር ግን እንደ ፕሮፌሰር ተብየው እርስዎም **አርእስትዎን** አሳምረው በመምጣት ቡድኑን ከተቀላቀሉአቸው በኋላ እንዲያውም እሳቸው ያላሉትን አስተያየቶች በጥሩ አማርኛ እያቀነባበሩላቸው፤ ተጨማሪ ስድቦችንም በማከል ከፍተኛ እርዳታ አበርክተዋል፡፡ እነዚህ ሁሉ ግን ከአንድ "**አስታራቂ ሽማግሌ ነኝ"** ከሚለው **የታሪክ ተንታኝ** የሚጠበቅ አይመስለኝም፡፡

አቶ **ጀዋር መሐመድ** ግለሰብ እንጂ የኦሮሞ ሕዝብ ውክልና የላቸውም፡፡ እናንተም ግለሰቦች እንጂ የክርስቲያኑም ሆነ የቤተ ክህነት ውክልና የላችሁም ማለት ነው፡፡ ስለዚህ፤ እያንዳንዳችን ያለንን ተቃውሞ ለይተን ማቅረብ መቻልን ከትምህርታችን በተጨማሪ እድሜአችንና ባህላችን ሊስተምረን ይገባል፡፡ ግለሰቦች እንደፈለጉ ተነስተው አንድን ብሔር አውዳሚ፤ ጨካኝ፤አረመኔ፤ወዘተ እያሉ ሕዝብን ከሕዝብ ጋር በማጋጨትና የጥላቻ መንፈስ በመሀከላቸው እንዲቆይ ለማድረግ ሲሞከሩ እንዴት ዝም ተብሎ ይታለፋል? ድርጊቱ የማይጠቅምና ጊዜው ያለፈበት መንገድ መሆኑን ሁላችንም ልንስማማበት ይገባል፡፡ ሁላችንም እስከዛሬ ድረስ በሕዝቦች ላይ ሲተረቱ በመጡት ስድቦች ምን ተጠቅመናል? ብለን እራሳችንን መጠየቅ አለብን ፡፡ ፕሮፌሰር ተብየው ጌታቸው ኃይሌ ከአለቃ አጽሜ አባባል እየወሰዱ "**ኦሮሞዎች ከአስርቱ ቃላት ውስጥ ከመጀመሪያው ትእዛዝ በስተቀር የተቀሩትን ዘጠኙን ትእዛዛት ከክርስቲያኖች በላይ ያከብራሉ"** ብለው በማወዳደር እየጻፉ፤ በሌላ ቦታዎች ደግሞ **"አረመኔ"** ሕዝብ ነው እያሉ በጭፍን ጥላቻ ሲሳደቡ ዝም ብለው ማለፍዎ ትዝብት ላይ አይጥልዎትምን? የኦሮሞ ሕዝብ ዛሬ የተለያዩ እምነቶችን (ዋቅፈታ፤ እስልምና፤ ክርስትና ወዘተ..) የሚከተል መሆኑ እየታወቀ፤ በጅምላ ግን **"አረመኔ"** ማለቱ ተገቢ ነውን? ፡፡ የኦሮሞውንና የሙስሊሙን ሕዝብ **አውዳሚነት፤ አረመኔነት፤ጨካኝነት** አምነው በመቀበል ሌሎችም አውዳሚዎች እንዳሉ ጠቀሱ እንጂ አባባላቸው ትክክል እንዳልሆነ፤ እንዲሁም፤ በተጠቀሱት ስድቦች ላይ በግልዎ የሰጡት አስተያየት አልነበረም፡፡ታዲያ እርስዎም ተቀብለዋል ማለት አይደለምን? ከሁሉም በላይ ደግሞ **"የታሪክ ታንታኝ ነኝ"** እያሉ ፕሮፌሰር ተብየው ጌታቸው ኃይሌ **"ኦሮምኛ ተናጋሪ ጎሣዎች"** በማለት የኦሮሞን ብሔርነት ለመካድ ሲሞክሩ እንዴት ዝም ብለው አለፉ? ለመሆኑ፤ **ሙስሊም** የሚባል የተለየ ጎሣ አለን? ሙስሊም ኦሮሞ፤ አማራ፤ ትግሬ፤ ጉራጌ፤ ሀዲያ፤ ወዘተ የሉምን? ሙስሌሞች ይቅርታ መጠየቅ አለባቸው ሲባል የትኞቹን ሙስሌሞች ማለት ነው? እነዚህን ለማስተካከል ባለመፈለግዎ

እንዲሁም፤ ተሳዳቢውን ግለሰብ የማይገባቸውን ክብር በመስጠት መከብዎ መብትዎ መሆኑን ባውቅም፤የእርስዎን የዳኝነት ብቃትና የግልዎን አቋም የማራመድ ችሎታ ከመሸርሸሩም በላይ አንድ ሕዝብ በጅምላ የሚሰደብበትን ሁኔታ ዝም ብሎ የሚያልፈውን ሰው "**የታሪክ ተንታኝ**' ነው ብዬ ከመቀበል ይልቅ አለመቀበሉ በሁሉም መልኩ ያረካኛል፡፡

ስለዚህ የጀመራችሁት መንገድ ትክክል ከለመሆኑም በላይ፤ ዲሞክራሲያዊ አስተሳሰቦችን ያላዘለ፤ እጅግ በጣም ኋላቀር በሆኑ አመለካከቶች የታጨቀ መሆኑን ልትገነዘቡት ይገባል፡፡በስድብና በተረት ያደገ አገር እንደሌለ ከናንተ በላይ ማንም ሊያውቅ አይችልም፡፡ ቢሆንማ ኖሮ ቀደም ሲል በነገሥታቶች ዘመን ለብዙ ዓመታት በሕዝቦች ላይ ሲካሄዱ በነበሩት የስድብ ዘመቻዎች አዎንታዊ ውጤቶች በተገኙ ነበር፡፡ በተቃራኒ ግን የተገኙት ውጤቶች በሕዝቦች መካከል መቃቃርንና ጥላቻን ማቆየት ናቸው፡፡በቅርቡም በአማራ ክልል፤ በባህር ዳር ከተማ በተካሄደው የየክልሎቹ የእስፖርት ውድድር ላይ በኦሮሞ እስፖርተኞች ላይ የተፈጸሙት አስነዋሪ ድርጊቶች የናንተና የመሰሎቻችሁ ዘመቻ ውጤቶች እንደሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡**"ስፖርት ለወዳጅነት"** የሚለው መፈክር ተገልብጦ ለጣላትነት መደረጉ እጅግ በጣም የሚገርም ከመሆኑም በላይ በእያንዳንዱ ተሳተፊዎች ላይ ትቶት የሚያልፈው አደጋ በቀላሉ የሚድን ቁስል እንዳልሆነ ታውቆ አስቸኳይ መፍትሔ ሊፈለግለት ይገባል፡፡በሥነሥርዓት እንግዶቼን አስተናግዳለሁ ብሎ ኃላፊነት የወሰደ ክልል ያ ሁሉ ሥነሥርዓት የጎደሉ ድርጊቶች ሲፈጸሙ አባሪ ተባባሪ ሆኖ ከመገኘቱም በላይ በሚድያው በኩል ትክክለኛ ዜና እንዳይተላለፍ ማድረጉ እጅግ በጣም ያሳዝናል፡፡ አሁንም ቢሆን ድርጊቶቹ ለማንኛውም ወገን የማይጠቅሙና የነፕሮፌሰር ተብዬው ትግል ውጤቶች መሆናቸው ታውቆ በሚመለከተው አካል የእርምት እርምጃ ይወሰዳል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

ስለዘላቂው ጉዳያችን ግን መወያየቱ በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ባለፈው ታሪካችን ላይ የነበሩት የአስተዳደር ሥርዓቶች በሕዝቡ ላይ እየደረሱ የመጡትን በደሎች ቆም ብለን በንጹህ ልቦና መርምረን፤ ይቅር ተባብለን፤ያለፉትን ሰቆቃዎች በቂም በቀል ደረጃ ላናስታውሰቸው ተማምለን፤በታሪክነቱ ለመጪው ትውልድ መተላለፍ የሚገባቸውን ዋና ዋና ነጥቦች ከመረጃ አንጻር በጋራ መርጠን ፤ ተገቢ ያልሆኑና ለወደፊቱ የጋራ እድገታችን እንቅፋት የሚሆኑትን ለመተው ተስማምተን ፤በአንድ ዓላማ ሥር ተሰልፋን ለሁላችንም ጠቃሚ ወደሆነው ወደ ልማት በጋራ መሄድ የነበረብን ወቅት እጅግ በጣም የዘገየ መሆኑን ተገንዝበን ፤በመጀመሪያ በፍጥነት ግን ወደ እርቅ መሄዱ ብቸኛ አማራጭ ይሆናል፡፡ የሰላሙን መንገድ በጋራ ለመጀመር ከልብ እንነሳ፡፡